


# መሪዎችን ማሳደግ

## አውደ ጥናት


ነቢያት

የቅጂ መብት © 2021 HTTP



## 1. በነቢያት ውስጥ ምን ምን መጻሕፍት ይካተታሉ?

የነቢያት መጻሕፍት በመባል የሚታወቁት የሚከተሉት ናቸው፡- ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሳሙኤል (1–2 ሳሙኤል በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ይወሰድ ነበረ)፣ ነገሥት (1–2 ነገሥት እንደዚሁም በመጀመሪያ አንድ መጽሐፍ ነበር)፣ ኤርሚያ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ እና “12ቱ” (ሆሴዕ፣ ኢዩኤል፣ አሞጽ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ሚክያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎኒያስ፣ ሐጌ፣ ዘካሪያስ፣ ሚልክያስ)። እነዚህ መጻሕፍት አንባቢው ከሕጉ መጻሕፍት ማለትም (ከዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኊልቊ፣ እና ከዘዳግም) ጋር በተወሰነ ደረጃ የተቀዱ ናቸው ብሎ ሊገምት ይችላል። በነቢያት ውስጥ ያሉትን ሁሉም መጻሕፍት ማለት ይቻላል ከሕጉ ብዙ ነገሮችን ወስደዋል። መጻሕፍቱ ከሕጉ በኋላ እየተጨመረ የሚሄድ ተፈጥሮዋዊ እድገት እያሳዩ የሚሄዱ ናቸው። ይህም ማለት በእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ቀጣዩ ምክንያታዊ እርምጃ ናቸው ማለት ነው። እነዚህ መጽሐፍት አንንባቢን ለጽሑፎች ያዘጋጃሉ ይህም (የብሉይ ኪዳን ሶስተኛውን ክፍል ማለት ነው)። በመጨረሻም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነቢያት በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል። እደዚሁም ደግሞ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አንባቢውን ከነቢያት ጋር የተወሰነ እውቀት እንዳለው ይገምታሉ። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ደግሞ በነቢያት የተጻፉትን ጽሑፎች እውነት እንደሆኑ አድርገው ይቀበላሉና።



## 2. የነቢያት አደረጃጀት እንዴት ነው?

**ነቢያት በሁለት ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ።** በነቢያት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ የመጻሕፍት ክፍሎች **የታሪክ** መጻሕፍት ናቸው። በዚህ የመጀመሪያ ምድብ ውስጥ ያሉት የነቢያት መጻሕፍት ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሳሙኤል ናቸው (1–2 ሳሙኤል በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ይቆጠሩ ነበር) እንደዚሁም ነገሥት (1–2 ነገሥት እነዚህም በመጀመሪያ አንድ መጽሐፍ ነበረ)። ሁለተኛው የነቢያት ቡድን **በዕብራይስጥ ቅኔ በተጻፉ ስብከቶች** የተሞሉ መጻሕፍት ናቸው። እነዚህም **የማብራሪያ** መጻሕፍት ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። በዚህ ሁለተኛ ክፍል ማለት በነቢያት ውስጥ አንዳንድ ትረካዎች (ማለትም ታሪኮች) ቢኖሩም (ለምሳሌ፣ የዮናስ መጻሕፍት ብዙ ትረካዎችን ያካትታሉ)፣ በአብዛኛው በዚህ ሁለተኛ ምድብ ውስጥ ይገኛሉ። እንደገናም በዕብራይስጥ ግጥም የተጻፉት ስብከቶችም ናቸው። በዚህ ሁለተኛ ምድብ ውስጥ የሚካተቱት የነቢያት መጻሕፍት ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳያይስ፣ እና "12ቱ" (ሆሴዕ፣ ኢዩኤል፣ አሞጽ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ሚክያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካሪያስ፣ ሚልክያስ) ናቸው።


በነቢያት ውስጥ ያሉትን የታሪክ መጻሕፍት የሚያተኩሩት በእግዚአብሔርና በእሥራኤል ድርጊት ላይ ነው። የታሪክ መጻሕፍት በተለየ መልኩ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ባለው ታማኝ እንክብካቤ እና ሕዝቡ ደግሞ ለእግዚአብሔር ታዛዥነት እና/ወይም አለምታዘዝ ላይ ያተኩራሉ። እነዚህ የታሪክ መጻሕፍት አብዛኛውን ጊዜ የሚያተኩሩት በነገሥታት ላይ ነው፣ ምክንያቱም ንጉሡ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ነውና። ስለዚህ የንጉሡ ድርጊቶች ልዩ ጠቀሜታ አላቸው። ሕዝቡ ንጉሡን ወደ መታዘዝ ወይም ወደ አለመታዘዝ ይከተሉታልና ወይም ይመራቸዋልና።


በነቢያት ውስጥ ያሉትን የታሪክ መጻሕፍት በዓለም ታሪክ ላይ ያተኮሩ አይደሉም። በሁሉም የዓለም ክፍሎች በመከናወን ላይ ያሉትን ሁሉንም ክስተቶች አያትቱምና። ይልቁንም በእሥራኤል ታሪክ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው እንጂ (ወይም ከጊዜ በኋላ በእሥራኤልና በይሁዳ ታሪክ) ላይ በማተኮር የሚዘግቡ ናቸው። ይህ የሆነው እግዚአብሔር ለተቀረው ዓለም ግድ ስለሌለው አይደለም። ይልቁንም እግዚአብሔር በአብርሃም ዘር በኩል ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ በረከትን እንደሚያመጣ ቃል ስለገባ ነው እንጂ (**ዘፍጥረት 12፡ 1–3** ይመልከቱ)። ለዚህም ነው በእሥራኤል ውስጥ የሚፈጸሙት ክንውኖች ልዩ ጠቀሜታ ያላቸው። አልፎ አልፎ ደግሞ በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት ጸሐፊዎች ትኩረታቸው በሌሎች ሀገራት ውስጥ እየተከናወኑ ባሉ ክስተቶችም ላይ ያነጣጠረ ነበር። ለምሳሌ ከሶሪያ የመጣ አንድ የጦር አዛዥ ከለምጽ

እንደ ተፈወሰ ተተርኳል (**2 ነገሥ 5** ይመልከቱ)። ኢየሱስ እንደ ተናገረው በዛ ዘመን ከለምጽ የተፈወሰው እሱ ብቻ ነው። ከእሥራኤል አንድም ሰው አልተፈወሰም ነበር (**ሉቃስ 4፡27** ይመልከቱ)። የዚህ ሶሪያዊ ሰው መፈወስ አላማው ለአሕዛብና ለእሥራኤል መልዕክት ለማስተላለፍ ታስቦ ነው። እምብዛም ባይሆኑም በሌሎች አገሮች ላይ የሚያተኩሩ እነዚህ ክፍሎች ልዩ ትኩረት ይፈልጋሉ። የእግዚአብሔር እቅዶች ለዓለሙ ሁሉ መሆናቸውን ያሳያሉና። በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝቦችም እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳለባቸው አልያም የእግዚአብሔርን እንክብካቤ እንደማያገኙ ያሳያሉ።

በነቢያት ውስጥ የስብከት እንድምታ ያላቸው መጻሕፍትም በነቢያት ውስጥ እንዳሉቱ የታሪክ መጻሕፍት ሁሉ በዋናነት በእሥራኤል ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። በነብያት ውስጥ እንዳሉት የታሪክ መጽሐፍቶች እነደተመለከትነውም፤ እዚህም ጋ እግዚአብሔር ስለሌላው ዓለም ደንታ ስለሌለው አይደለም። ይልቁንም የእሥራኤላውያን ለቃል ኪዳኑ መታዘዛቸው የእግዚአብሔር በረከት ወደ ተቀረው ዓለም እንዲደርስ ቁልፍ ነገር ስለሆነ ነው እንጂ።

ኢየሱስና ሐዋሪያቱ በነቢያት ውስጥ ከነበሩት የመጀመሪያው የመጻሕፍት ምድብ ውስጥ የተፈጸሙትን ክንውኖች እንዴት እንደሚተረጎም ማሰቡ ለሰባኪው ወይም ለአስተማሪው ትልቅ እገዛ ነው። በተጨማሪም ኢየሱስና ሐዋሪያቱ በሁለተኛው የነቢያት ክፍል ውስጥ የሚገኙትን ስብከቶች ደግሞ እንዴት እንደተረጎሙ ማጤን አስፈላጊ ነገር ነው።






## 3. የእሥራኤል አሳዛኝ ታሪክ በተስፋይቱ ምድር

የሙሴ መጽሐፍ የሚያበቃው እሥራኤላውያን ወደ ተስፍይቱ ምድር ሊገቡ በተቃረቡበት ጊዜ ነው። አንባቢው እሥራኤል ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንደሚመላለስ ተስፋ ያደርግ ይሆናል። ይሁን እንጂ የሙሴን መጽሐፍ በቅርብት ማንበብ ለአንባቢው እሥራኤላውያን ያሳለፉትን የሐሰት አምልኮና የአመፀኝነት ታሪክ እንዲረዳ ያዘጋጀዋል። እንደዚሁም ሙሴ እሥራኤላውያን እግዚአብሔርን እንደማይታዘዙና በምድሪቱም ፀንተው እንደ ማይቆዩ ተንብዮ ነበር (**ዘዳግም 4፡15–31** ይመልከቱ)። አንባቢው ነቢያትን ሲያነብ እሱ ወይም እሷ የሙሴ ትንቢት በኢያሱ፣ በመሳፍንት፣ በሳሙኤል እና በነገሥታት ላይ ሲፈጸም መመልከት ይቻላል። ገና ከጅምሩ እሥራኤል ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ለመራመድ ፈቃደኛ አልሆነችም (**ኢያሱ 7** ይመልከቱ)። ምንም እንኳን እግዚአብሔር እሥራኤልን ደጋግሞ ቢያድንም፤ እሥራኤላውያን ግን ደጋግመው በአለመታዘዝ ይመላለሱ ነበር። እሥራኤል ሀሰተኛ አማልክቶችን ታመልክ ነበርና። እግዚአብሔር ደግሞ እሥራኤልን ወደ ንስሀ እንዲጠሩ ነቢያትን ላከ። ይሁን እንጂ እሥራኤል ለመስማት ፈቃደኛ አልሆነችም። በመጨረሻም ልክ ሙሴ ትንቢት እነደተናገርውም እሥራኤላውያን ከምድሪቱ ተባረሩ። ማለትም ልክ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ልጅ (አዳም) ከእግዚአብሔር ከገነት እንደተባረረ፤ የእግዚአብሔር "ልጅ" የሆነው እሥራኤልም እግዚአብሔር ባዘጋጀው ቦታ መቆየት አልተቻለውም።

በብሉይ ኪዳን እሥራኤልን ለማመልከት የተለመደ ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለው የወይን ግንድ የሚለውን ምሳሌ ነው (**መዝሙር 80፡8–14፤ ኢሳይያስ 5፡2፤ ኤርምያስ 2፡21፣ 5፡10፣ 6፡9 እና 8፡13** ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ደግሞ ከገበሬ ጋር ተነጻጽሯል። እግዚአብሔር ወይኑን የተከለው በተዘጋጀ ምድር ላይ ነበር (**ኢሳይያስ 5፡2** ይመልከቱ)። ለአጭርም ጊዜ ቢሆን ወይኑ እንደማደግ ብሎ ነበር (**1 ነገሥት 4፡25** ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ወይኑ ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ (**ኢሳይያስ 5፡2** እና **ሆሴዕ 10፡1** ይመልከቱ)። በመጨረሻም ወይኑ ከሥሩ ተነቀለ ምድሪቱም ባዶዋን ተቀመጠች (**መዝሙር 80፡8–14** ይመልከቱ)። ይህ አሳዛኝ የእሥራኤል ታሪክ የተፈጸመው በእግዚአብሔር መልካም ቦታ ነው። በ**ማቴዎስ 21፡33–42**፣ **ማርቆስ 12፡1–10**፣ በ**ሉቃስ 13፡5–7** እና **20፡9–17** ላይ ያሉትን የኢየሱስ ምሳሌዎች ይህን አሳዛኝ ታሪክ ለሰዎች ለማስታወስ የታሰቡ ናቸው። ሆኖም ግን የእግዚአብሔር "የወይን ተክል" ታሪክ በፍሬ አልባነት አያበቃም። ኢየሱስ እንደ እሥራኤልም ከወይን ግንድ ጋር ሲነጻጽር እንመለከታለንና (**ዮሐንስ 15** ይመልከቱ)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ኢየሱስ ራሱን "እውነተኛ የወይን ግንድ" ሲል ጥርቷል። ከእሥራኤል በተለየ ሁኔታ ኢየሱስ ሁልጊዜ መልካም ፍሬ ያፈራል (**መዝሙር 1፡3** ይመልከቱ)። እንደዚሁም በክርስቶስ ያሉቱ ሁሉ ደግሞ መልካም ፍሬ ያፈራሉ (**ገላትያ 5፡22–23** ይመልከቱ)።



## 4. የኢያሱ መጽሐፍ – ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት

የኢያሱ መጽሐፍ የትረካ መጽሐፍ ነው (ማለትም፤ ታሪክ ነው)። ደግሞም ከነቢያት መጻሕፍት የመጀምሪያ መጽሐፍም ነው። እንደገና ለማስታውስ ያህል ነቢያት በሁለት ምድቦች ሊከፍሉ ይችላሉ። የመጀመሪያው ምድብ የታሪክ ምጻሕፍትን ያካትታል። ሁለተኛው ምድብ የማብራሪያ መጻሕፍትን ይይዛል። እንግዲህ መጽሐፈ ኢያሱ በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ ከመጀምሪያው የመጽሐፍት ምድብ የመጀምሪያው መጽሐፍ ነው ማለት ነው።

መጽሐፈ ኢያሱ ከነቢያት ውስጥ የመጀመሪያ መጽሐፍ እንደመሆኑ መጠን በነቢያት ውስጥ ካሉት መጻሕፍት መካከል ልዩ ቦታ አለው። ይህ መጽሐፍ በሕግ (በሙሴ መጽሐፍት) እና በነቢያት መካከል እንደ **መሸጋገሪያ** ያገለግላል። ይሁን እንጂ መጽሐፈ ኢያሱ በአዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል (ነቢያት) ውስጥ የሚገኝና ደግሞም በዲሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ (ኢያሱ) ላይ የሚያተኩር ቢሆንም አሁንም በአብዛኛው በመጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው ክፍል ጋር የተያያዘ ነው። ሙሴ በመጽሐፉ እንደ ጀመረው ኢያሱም ተመሳሳይ ታሪክ እየተናገረ ነው። የኢያሱ መጽሐፍ በሙሴ መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ አሁንም በእሥራኤል ሕዝብ ላይ እንደሚሠራ ግልጽ ያደርጋል (**ኢያሱ 8፡32** ይመልከቱ)።

የመጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊ መጽሐፉ ውስጥ አልተጠቀሰም። ኢያሱም እንደ ጻፈው የሚገልጽ ፍንጭ አይሰጥም። ኢያሱ እሥራኤላውያን በምድሪቱ ላይ ያገኙትን ድል በዝርዝር ለመመዝገብ ፍላጎት ቢኖረውም ቅሉ (**ኢያሱ 18፡8** ይመልከቱ) መጽሐፉን ግን በሙሉ መጻፉን እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ይህም ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም የኢያሱ መጽሐፍ የኢያሱ መሞት ይናገራልና (**ኢያሱ 24፡29–31** ይመልከቱ)። ጸሐፊው በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ስለተመዘገቡት ክንውኖች የተናገረበትን መንገድ መሠረት በማድረግ ስንመለከት የመጽሐፉን ክፍሎች የተጻፉት በመጽሐፉ ውስጥ ከተመዘገቡት ነገሮች በዙም ሳይቆይ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል፤ ደራሲው ኢያሱ እንደ መታሳቢያ ስለተከላቸው አሥራ ሁለቱ ድንጋዮች ሲናገር "እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ አሉ" ይላል (**ኢያሱ 4፡9** ይመልከቱ)። ደግሞም ደራሲው መጽሐፉን ሲጽፍ ረዓብ በሕይወት እንደነበረች ተናግሯል (**ኢያሱ 6፡25** ይመልከቱ)። ደራሲው በኖርበት ዘመን ሁሉ ክስተቶቹ በትክክል እንደተከሰቱ አንባቢው እንዲያምን እንደሚፈልግ ግልጽ ነው። ለዚህም ነው በመጽሐፉ ውስጥ በተመዘገቡት ክንውኖች እና መጽሐፉ በተጻፈበት ወቅት መካከል ብዙ የተያያዙ ነገሮችን ያደረገው (**ኢያሱ 7፡26** ይመልከቱ)። እነዚህን ሁሉ ነገሮች በመጽሐፉ ውስጥ የተመዘገቡትን

ከንውኖች በተገለጹበት መንገድ የተፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ያገለግላሉ። ለምሳሌ ፀሐፊው ቦታዎች በተወሰኑ ስሞች እንደሚጠሩ ያብራራል (**ኢያሱ 5፡9** ይመልከቱ)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉት ሁሉም ደራሲዎች የመጽሐፈ ኢያሱም ጸሐፊ እግዚአብሔርን እንደሚወድ እና በእግዚአብሔርም ላይ ታላቅ እምነት እንደነበረው ግልጽ ነው። ደግሞም ደራሲው አንባቢዎቹ እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያደርጉ የሚፈልግ ይመስላል።

ኢያሱ ታላቅ ሰው ነበር፤ ነገር ግን በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ "እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ" ተብሎ በጭራሽ አልተገለጸም (**ዘዳግም 18፡5–19 እና 34፡9–12** ይመልከቱ)። ኢያሱ እግዚአብሔር አስነሳዋለሁ ያለው ነቢይ አይደለም። አንባቢው የኢያሱን ታማኝነት እንደሚያደንቅ ሁሉ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላ መሪ ማለትም "እንደ ሙሴ" የሆነ ነቢይ እየጠበቀ ነው። ይህም ማለት ይህ የሚመጣው ነቢይ እንደ ሙሴ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት የሚያይና እንደ ሙሴ ደግሞ ብዙ ምልክትና ድንቅ የሚያደርግ ነው ማለት ነው። ያም ነቢይ ጌታችን ኢየሱስ ነው!

ኢያሱ የሙሴ ረዳት ነበር (**ኢያሱ 1፡1** ይመልከቱ)። "ሙሴ እጁን ስለጫነበት የጥበብ መንፍስ የተሞላ ሰው ነበር" (**ዘዳግም 34፡9** ይመልከቱ)። እግዚአብብሔር ኢያሱን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የዮርዳኖስ ወንዝ ተሻግሮ ወደ እግዚአብሔር መልካሚቱ ምድር እንዲመራ አዘዘው። በ **1 ነገሥት 6፡1** በመመስረት ስንመለከት ዘፃአት የተከናወነው በ1446 ዓክልበ አካባቢ ነው። ይህም ማለት ኢያሱና ሕዝቡ ከነዓንን ድል አድርገው መውረስ የቻሉት ከ40 ዓመታት የምደረበዳ ጉዞ በኋላ ነው ማለት ነው። በዚሁ መሠረት የከነዓን ወረራ የተካሄደው በ 1406 ዓክልበ አካባቢ ነው ማለት ነው።

ኢያሱ ታላቅ መሪ ነበር። የእሥራኤል ሕዝብ "በኢያሱ ዘመን ሁሉ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር" (**ኢያሱ 24፡31** ይመልከቱ)። በዚህ መንገድ ኢያሱ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ክርስቶስ እንደ ኢያሱ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር መልካም ቦታ መርቷቸዋል፤ እግዚአብሔርንም እንዲታዘዙ ረድቷቸዋል። እንደ ኢያሱ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ግን ይህን ፍጹም በሆነ መንገድ ማድረግ ይችላል። ኢያሱ ደግሞ ሌላም ድክመት ነበረበት፤ ማለትም የእርሱ አመራር ጊዜያዊ ነበርና። ደግሞም ሞት ከዚህ በላይ እንድያገለግል ከለከለው። ኢየሱስ ግን ቢሞትም ሞትን አሸንፎ ተንሥቷል። ኢየሱስ ዘላለም ነዋሪ ነውና፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ምንግዜም ከእግዚአብሔር መሪነት ውጪ ሊሆኑ አይችሉም። ኢየሱስ

ደግሞ ኢያሱ ማድረግ ያልቻለውን ሌላ ነገር ማድረግ ችሏል። ይህም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዲችል ልባቸውን መለውጥ ይችላልና (**ዮሐንስ 14፡15–31** ይመልከቱ)። ስለዚህ የኢያሱ አማራር የኢየሱስን አመራር በትንሹ ምሳሌ ነበር ማለት ነው።

ምንም እንኳን መጽሐፈ ኢያሱ በኢያሱ ስም ቢጠራም እና የኢያሱንም አመራርና ድርጊት ቢገልጽም፤ ስለ ኢያሱ ብቻ የሚናገር መጽሐፍ አይደለም። መጽሐፉ ከኢያሱ በተጨማሪ ስለ እሥራኤል ሕዝብ እና እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባላቸውን ምድር ርስት በተመለከተም ይናገራል። ፀሐፊው እሥራኤልውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባታቸውንና ያስመዘገቡዋቸ ድሎችና ሽንፈቶች በምድሪቱ ሲያልፉና ምድሪቱንም ሲከፋፈሉ የነበረውን ሁናቴ በሙሉ በዝርዝር በጥንቃቄ መዝግቧል። የፀሐፊው ቃላቶች የእሥራኤል ስኬቶችና ውድቀቶች ሁሉም በቀጥታ ከእሥራኤል መታዘዝ ወይም ለእግዚአብሔር ሕግ ከአለመታዘዝ (በሙሴ መጽሐፍ ተመዝግበው የሚገኙትን ሁሉ ማለት ነው) ጋር የተገናኙ መሆናቸውን ያሳያሉ። ደራሲው አንባቢዎቹ ስለ እሥራኤል ሽንፈቶች እና ድሎች ከሕጉ አንጻር በጥንቃቄ እንዲያስቡ የሚፈልግ ይመስላል።

የኢያሱ ጸሐፊ በግልጽ እግዚአብሔር ምድሪቱን ለእሥራኤል ሲሰጥ ታማኝ አምላክ እነደሆነ አንባቢዎቹ እንዲረዱ ይፈልጋል። ደግሞም ደራሲው አንባቢዎቹ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ክፍል ሲጠብቅ እንዲያዩ ይፈልጋል (ለምሳሌ **ኢያሱ 10፡14** ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር ታማኝነት ደግሞ በ **ኢያሱ 21፡43–45** ተጠቃሷል።


> እግዚአብሔርም ይሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር ሁሉ ለእሥራኤል ሰጠ፤ ወረሷአትም፣ ተቀመጡባትም። እግዚአብሔርም ለአባቶቻቸው እንደ ማለላቸው በዙሪያቸውም ካሉት አሳረፋቸው፤ ከጠላቶቻቸውም ሁሉ ይቋቋማቸው ዘንድ ማንም ሰው አልቻለም፤ እግዚአብሔርም ጠላቶቻቸውን ሁሉ በእጃቸው አሳልፎ ሰጣቸው። እግዚአብሔርም ለእሥራኤል ቤት ከተናገረው መልካም ነገር ሁሉ ተፈጸመ እንጂ ምንም አልቀረም።

የመጽሐፈ ኢያሱ እግዚአብሔር የራሱ ድርሻ የሆነውን የቃል ኪዳኑን ክፍል በሚገባ እንደጠበቀ ያሳያል። ሁሉንም የእሥራኤል ድሎች እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዴት እንደ ሚዋጋ ማሳያዎች ናቸው። ይሁን እንጂ እሥራኤል ግን የቃል ኪዳኑን ክፍል አልጠበቀም። እሥራኤልውያን ከእግዚአብሔር ጋር ባደረጉት "ጋብቻ" ውስጥ ብዙ ጊዜ **መንፈሳዊ ምንዝርና** ፈጽመዋል። እስራኤልውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡበት ጊዜ አንስቶ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አልጠበቁም። ከዚህም ባሻገር፣ አንዳንድ ሰዎች አሁንም ሌሎች አማልክቶችን ያመልኩ ነበር (**ኢያሱ 24፡ 14** ይመልከቱ)።

በኋላም ነቢያት እሥራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ አልታዘዙም ብለው አውጀዋል። ለምሳሌ በ **ሆሴ 9፡15** ላይ እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፡- “ክፋታቸው ሁሉ በጌልገላ አለ፤ በዚያ ጠልቻቸዋለሁ፤” እሥራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ከተሻገሩ በኋላ የቆሙበት የመጀምሪያ ቦታ ጌልጌላ ነበር (**ኢያሱ 5፡8** ይመልከቱ)። እግዚአብሔር በሆሴ የተናገራቸው ቃል እንደሚያስረዳው ከሆነ እሥራኤላውያን በምድሪቱ ላይ ባደረጉት በዚህ በመጀምሪያ የጌልጌላ እረፈት እንኳን ታዛዦች አልነበሩም።

ነገር ግን እሥራኤል በፍጹም ታዛዥነት መመላለስ ያልቻሉበት ምክንያት እሥራኤልን ብቻ ሳያሳርፍ አልቀረም። እንደዚሁም ደግሞ ኢያሱንም ሊያሳርፋቸው እንዳይችል አድርጎታል። ምንም እንኳን የእሥራኤል መሪ ቢሆንም ቅሉ ነገር ግን ልባቸውን የመለወጥ ኃይል አልነበርውምና። ኢያሱም ደግሞ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ጥበብ የመፈለግ ዝንባሌ አልነበረውም (**ኢያሱ 9** ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲታዘዙ – የሕዝቡንም ልብ ለመለወጥ ኃይል ያለው መሪ አዲስ እና የተሻለ መሪ ያስፈልግ ነበር። ያም መሪ ኢየሱስ ነው።

የዕብራውያን ፀሐፊ (በአዲስ ኪዳን) አንባቢዎቹ ኢያሱ ሕዝቡን “ዕረፍት” ሊሰጣቸው እንዳልቻለ እንዲያጤኑት ይፈልጋል፡- “ኢያሱ አሳርፎአቸው ኖሮ ቢሆንስ ከዚያ በኋላ ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር። እንግዲህ የሰንበት ዕረፈት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል። ወደ ዕረፍቱ የገባ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና” (**ዕብራውያን 4፡ 8–10**) ይላል። ይህም ማለት ኢያሱ ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር መልካም ቦታ ቢያመጣም የሚያስፈልጋቸውን የመጨረሻ ዕርፍት ግን ሊሰጣቸው አልቻለም። ስለዚህ እሥራኤላውያን በእውነት በእግዚአብሔር መልካም ቦታ “እንዲያርፉ” ከተፈለገ ከኢያሱ የተሻለ መሪ ያስፈልጋቸው ነበር።





## 5. መጽሐፈ መሳፍንት – ያለ ንጉሥ ሕይወት

መጽሐፈ መሳፍንት የትረካ መጽሐፍ ነው (ማለትም ታሪኮችን የሚተርክ ነው)። እንደ አብዛኞቹም የትረካ መጻሕፍት በዚህ መጽሐፍ ውስጥም ከአንድ በላይ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች አሉ። እንደዚሁም ደግሞ በመሳፍንት 5 ላይም ረጅም ግጥም አለ። ስለዚህ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ዓይነት ጽሑፎች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ መረዳትታቸው አስፈላጊ ነገር ነው።

መጽሐፈ መሳፍንት ከነቢያት ሁለተኛው መጽሐፍ ነው። የመጽሐፈ መሳፍንት ደራሲ (ወይም ደራሲዎች) አልተጠቀሰም ወይም አልተጠቀሱም፤ ነገር ግን ደራሲው የኖረው በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ከተገለጸው ጊዜ በኋላ እንደሆነ ግልጽ ነው። ደራሲው የእምነት ሰው ነው፤ በመሆኑም የሚጽፋቸው ነገሮች በትክክል እንደተፈጸሙ አንባቢ እንዲያውቅ ይጥራል። ለዚህም ነው በእርሱ ዘመን የተፈጸሙትን ክንውኖች በመሳፍንት ጊዜ ከተፈጸሙት ክንውኖች ጋር የሚገናኙ አንዳንድ ዝርዝሮችን ያካተተው (**መሳፍንት 1፡21** ይመልከቱ)። አብዛኛው የመጽሐፉ ክፍሎች የተጻፉት በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ከተገለጹት ክንውኖች በኋላ ብዙም ሳይቆይ ቢሆንም ነገር ግን ሙሉውን የመሳፍንት መጽሐፍ አሁን ባለው ቅርጽ እሥራኤልውያን ወደ ምርኮ ከገቡም በኋላ አልተጠናቀቀም ነበር (**መሳፍንት 18፡30** ይመልከቱ)። ይህ መጽሐፍ በግዞት ዘመን ለነበሩት እሥራኤላውያን ከእነርሱ በፊት የነበሩት እሥራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡበት ጊዜ አንስቶ ለእግዚአብሔር ታዛገኞች እንዳልነበሩ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው።

ደራሲው ኢያሱ ከሞተ በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ የተከናወኑትን ሁኔታዎች ገልጿል (**መሳፍንት 1፡1** ይመልከቱ) እንደዚሁም በእሥራኤል ንጉሥ ከመሾሙም በፊት የተከናወኑ ነገሮችን ጽፏል (**መሳፍንት 17፡6፣ 18፡1፣ 19፡1 እና 21፡25** ይመልከቱ)። ይህም ማለት መጽሐፈ መሳፍንት በመጽሐፈ ኢያሱ ከተገለጸው ጊዜ በኋላ እና በ 1ኛ እና በ 2ኛ ሳሙኤል ከተገለጸው ጊዜ በፊት በእሥራኤል ውስጥ የተፈጸሙትን ሁኔታዎችን ይዘረዝራል ማለት ነው። እንደዚሁም መጽሐፈ ሩት ውስጥ የተገለጹት ክንውኖችም የተፈጸሙት በመሳፍንት ላይ በተገለጸው ዘመን ውስጥ ነው። ሆኖም መጽሐፈ መሳፍንትና መጽሐፈ ሩት በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተለያዩ መጻሕፍት ናቸው። መጽሐፈ መሳፍንት ከነቢያት ሁለተኛው መጽሐፍ ነው። ከኢያሱ በኋላ እና ከ 1–2 ሳሙኤል እና 1–2 ነገሥት በፊት ይገኛል። መጽሐፈ ሩት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ድርሰናት ወይም ጽሑፎች ከሚባሉት ክፍል የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው። በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት በጣም ጥንታዊ የመጻሕፍት ዝርዝሮች ውስጥ መጽሐፈ ሩት ከመዝሙረ ዳዊት በፊት ተቀምጧል። የመጻሕፍቱ አቀማመጥ **በብሉይ ኪዳን ቀኖና** ውስጥ በእነዚህ ሁለት መጻሕፍት መካከል ያለው ልዩነት ብቻ አይደለም። መጻሕፍቱ በጣም የተለያየ መልዕክት ያዘሉም ናቸው። መጽሐፈ መሳፍንት

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ተደጋጋሚ ውድቀት ይገልጻል እንደዚሁም ደግሞ የሚጨርሰው በጣም አሉታዊ በሆነ መንገድ ነው። ጸሐፊው እሥራኤል ምንም ንጉሥ እንደሌላቸውና ሕዝቡም የፈልጉትን ያደርጉ እንደነበረ አንጻዖት በመስጠት ይናገራል (**መሳፍት 17፡6 ፣ 18፡1፣ 19፡1** እና **21፡25** ይመልከቱ)። በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ያሉት ሰዎች ከጥቂት መሪዎች እና ከጥቂት ሁኔታዎች በስተቀር በአጠቃላይ እግዚአብሔርን አይታዘዙም ወይም ትእዛዛቱንም አይከተሉም ነበር። በተቃራኒው ደግሞ መጽሐፈ ሩት ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያደርጉዋቸው ስለታዛዥ ምርጫዎች ይገልጻል እንደዚሁም መጫረሻውም በጣም አዎንታዊ በሆነ መንገድ ይደመደማል። እንዳውም መጽሐፉ የሚያበቃው በንጉሥ ዳዊት ላይ በማተኮር ነው። ንጉሥ ዳዊት በጣም አስፈላጊ ሰው ነውና፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከዳዊት ልጆች አንዱ ለዘላለም በዙፋኑ ላይ እንደሚቀመጥ ለዳዊት ቃል ገብቶለታል (**2 ሳሙኤል 7፡ 1–17** ይመልከቱ)። በዚህ ትንቢት ለዳዊት የተነገርው ስለኢየሱስ ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር የዘላለም ንጉሥ ነውና።

መጽሐፈ መሳፍንት የእግዚአብሔር ሕዝብ በሲና ተራራ በእግዚአብሔርና በአባቶቻቸው መካከል የተገባውን ቃል ኪዳን በመታዘዝ እየኖሩ እንዳልነበሩ በግልጽ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። የእሥራኤል ሕዝብ በመደጋገም በኃጢአትና በጣዖት አምልኮት ውስጥ ወደቀዋል። ስለዚህ የመሳፍንት መጽሐፍ እስራኤልውያን ታማኝ እንዳልነበሩ የሚያሳይ መጽሐፍ ከመሆኑም በላይ ቃል ኪዳናቸውን ማፍረሳቸውን የሚያስገነዝብ መጽሐፍ ነው። እንዲያውም በመጽሐፈ መሳፍንት መግባደጃ ላይ (**መሳፍንት 17–21** ይመልከቱ)፤ የእሥራኤል ኃጢአት ሆን ተብሎ የተገለፀው አንባቢው የሰዶምና የገሞራን ኃጢአት በሚያስታውስበት መልኩ ነው። አንባቢው ስለ እግዚአብሔር ሰዎች ኃጢአት ሲያነብ ስለ ሰዶምና ገሞራ ማሰብ አለበት። እሥራኤላውያን በመሳፍንት ዘመን በኃጢአት ምክንያት እንደጠፍት እንደነዚያ ሁለት ከተሞች ነበሩ (**ዘፍጥረት 18፡22–29** ይመልከቱ)! ነገር ግን የመሳፍንት መጽሐፍ የሕዝቡን ታማኝነት የጎደለው ድርጊት አጽንዖት ቢሰጥም በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን ቸርነት፣ ምሕረት እና ታማኝነት በማጉላት ይናገራል። የሕዝቡንም ጩኸት እየሰማ ከጠላቶቻቸውም ዘወትር ነፃ እንደሚያወጣቸው ደግሞ ይናገራል።

በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ በተገለጸው መሠረት የእግዚአብሔር ሕዝብ ነፃ ይወጣ የነበረው እግዚአብሔር **መሪዎችን** ያስነሳላቸው ስለነበር ነው። እነዚህም መሪዎች በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ “ፈራጅ” ወይም “አዳኝ” ተብለው ይጠሩ ነበር። ፍራጅ የሚለው (የእንግሊዝኛው) ቃል አንዳንድ ጊዜ ለመፍርድ ከተቀመጡ ዳኞች ይያያዛል ይሁን እንጂ እነዚህ ፈራጆች ስራቸው የፍርድ ቤት ዓይነት ሥራ አልነበረም። በመሳፍንት ዘመን የነበረ አንድ ፈራጅ በዋንኛነት እሥራኤልን ከጠላቶቹ ነፃ ለማውጣት ሕዝቡን እንዲመራ እግዚአብሔር የሚያስነሳው ጠንካራ መሪ ነበር። እግዚአብሔር ያስነሳው ፈራጅ (አዳኝ) በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔር እሱን ተጠቅሞ ሕዝቡን ያድን ነበር። ይሁን እንጂ ፈራጁ

**ከሞተ በኋላ** ሕዝቡ በፍጥነት ይሸነፋል እናም እንደገና በጠላቶቻችው እጅ ይወድቁም ነበር (**መሳፍንት 2፡ 16–19** ይመልከቱ)። ስለዚህ በኃጢአት መውደቅን፣ እንደገና መጥፋትን እና ነፃ መውጣት ኡደት ይጀመር ነበር። በዚሁም መሠረት ሕዘቡ የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ይጮኻል እግዚአብሔርም ሰምቶ ፈራጅ ያስነሳላቸዋል፣ ዳኛውም ደግሞ ሕዝቡን ይታደጋል። የፈራጁ መሞት ለእሥራኤል ሕዝብ ትልቅ ችግር ነበር ምክንያቱም ሞት አዳኙ እሥራኤል ለረጅም ዘመናት እንዳያድን ይከለክለው ነበርና። በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው እግዚአብሔር የቀባው መሪ ፈጽሞ ባይሞት ኖሮ ይህ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ታላቅ እርዳታ ይሆን ነበር! ነገር ግን በኃጢአት ምክንያት ሰዎች ሁሉ ይሞታሉና። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝቦች መዳን ሁልጊዜ አጭር ነበር። በመሆኑም ይህ መጽሐፍ ደግሞ የማይሞት መሪ እንዲመጣ ፍላጎትን የሚጭር መጽሐፍ ነው። ያም መሪ በሰዓቱ መጣ። ስሙም ኢየሱስ ነው! የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ለማዳን **ዘወትር በሕይወት** ይኖራልና (**ዕብራውያን 7፡25** ይመልከቱ)!

መጽሐፈ መሳፍንት በእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ በእርግጥ የሚመራው ሰው እንደሚያስፈልገው ያሳያል። የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ ከሌለው በአለመታዘዝ ይመላለሳል ብሎም በጠላቶቹ ይሸነፋል። ስለዚህ መጽሐፈ መሳፍንት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ፍሪሃ እግዚአብሔር ያለው መሪ ወይም ንጉሥ እንደሚያስፈልገው ያሳያል! ደግመን ለማስታውስ ያህል፤ መጽሐፈ መሳፍንት በእግዚአብሔር ሕዘብ መካከል እግዚአብሔርን የሚፈራ ንጉሥ የመፈለግ ፍላጎት ለመፍጠር የታሰበ መጽሐፍ ነው። የመጽሐፈ መሳፍንት ፀሐፊም ፍሪሃ እግዚአብሔር ያለው ንጉሥ እንደሚፈልግ ግልጽ ነው። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው የሚያድን ፍሪሃ እግዚአብሔር ያለው ንጉሥ ብቻ ነውና። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ደግሞ እንዲታዘዙ ማድረግ የሚችለው ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ንጉሥ ብቻ ነው። አሁን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲህ ያለውን ንጉሥ እስኪመጣ ድረስ እየጠበቁ አይደለም። ምክንያቱም ኢየሱስ መጥቷልና! የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ጠላቶች ድል በመንሳት የእግዚአብሔር ሕዝብ በታዛዥነት እንዲሄዱ አድርጓል። **በዚህ ዘመን ደግሞ የእግዚአብሔር ቦታ የያዘ ንጉሥ አለ፤ ንጉሡንም የሚከተል ሁሉ በፊቱ ትክክል የመሰለውን ሁሉ ያደርጋል ማለት ነው!**

መጽሐፈ መሳፍንት አንባቢን ለ 1–2 ሳሙኤል መጽሐፍ ያዘጋጃል (እነዚህ መጽሐፍት በመጀምሪያ በዕብራይስጥ የተዋሃዱና እንደ አንድ መጽሐፍ ነበሩ)። አንባቢውም መጽሐፈ መሳፍንትን አንብቦ የሚጨርሰው በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጹትን ፈራጆች ንጉሥን መናፈቃቸውን እያስተዋለ ነው። 1 ሳሙኤል ደግሞ ያ ንጉሥ እንደ ሚመጣ ያስረዳል።


ISRAEL

## 6. መጽሐፈ ሳሙኤል– ሳሙኤል፣ ሳኦል እና ዳዊት

መጽሐፈ ሳሙኤል የትረካ መጽሐፍ ነው (ማለትም ታሪካዊ ነው)። እንደ አብዛኛዎቹም የትረካ መጽሐፍት በዚህም መጽሐፍ ውስጥም ደግሞ ከአንድ በላይ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች አሉ። እንደዚሁም ደግሞ በ **1 ሳሙኤል 2፡1–10፣ 2 ሳሙኤል 1፡19–27 እና 22፡1–23፡7** ላይ ረጃጅም ግጥሞች አሉ። እነዚህ ግጥሞች በተለይም በሳሙኤል መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ያሉትን ግጥሞች ጠቃሚ ናቸው። ግጥሙም በተደጋጋሚ የጽሑፉን ዋና ነጥብ የሚያጎላ ሲሆን ስለ ክርስቶስ ዝርዝር ጉዳዮችን ያካትታል። በሳሙኤል መጀምሪያና መጨረሻ ላይ ያሉትንም ግጥሞች ቢሆን እንደዚሁ ናቸው። ሰባኪዎችና አስተማሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ዓይነት ጽሑፎች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ መረዳታቸው አስፈላጊ ነው።

ቀደም ተብሎ እንደ ተገለጸው 1–2 ሳሙኤል በመጀመሪያ በዕብራይስጥ አንድ መጽሐፍ ነበረ። ስለዚህ 1–2 ሳሙኤል እንደ አንድ መጽሐፍ ማለትም  መጽሐፈ ሳሙኤል ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ሳሙኤል ከነቢያት ዘርዝር ውስጥ ሦስተኛ መጽሐፍ ነው። በነቢያትም ውስጥ በመጀመሪያው የመጻሕፍት ምድብ ውስጥ ይገኛል። እንደገና ለማስታወስ ያህል በነቢያት ውስጥ ሁለት ዓይነት መጻሕፍት አሉ፡- የታሪክ መጻሕፍትና የሐተታ መጻሕፍት። ሳሙኤል የታሪክ መጽሐፍ ነው። ይሁን እንጂ ደራሲው ደግሞ ማን እንደሆነ አልተጠቀሰም።

ሳሙኤል በእሥራኤል ውስጥ መሳፍንት ይመሩበት የነበረውን ዘመን መጨረሻ እና ነገሥታት እሥራኤልን መምራት የጀመሩበት ጊዜ ደግሞ መጀመሩን ያበስራል።

መጽሐፈ ሳሙኤል የሚጀምረው የሳሙኤልን ልደት በመናገር ነው (1 ሳሙኤል 1)። ሳሙኤል እሥራኤልን የመራ የመጨረሻው ፈራጅ ነበር። ሳሙኤል ፈራጅ ብቻ ሳይሆን ደግሞም ነቢይ ነበር። ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ቃል አቀባይ በመሆን በእሥራኤል የመጀመሪያዎቹን ሁለት ነገሥታት የቀባ ነቢይ ነው። ሳኦልን በእሥራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ ቀብቷል (**1 ሳሙኤል 8–10** ይመልከቱ)፤ እንደዚሁም ዳዊትንም በእሥራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ የቀባው ነቢዩ ሳሙኤል ነው (**1 ሳሙኤል 16፡1–13** ይመልከቱ)።

በ **1 ሳሙኤል 2፡1–10** ላይ አንድ ጠቃሚ ግጥም አለ። ግጥሙም የሐና የሳሙኤል እናት ፀሎት ነው። ይህ ግጥም አስፈላጊ የሆነበት ዋና ምክንያት እግዚኢአብሔር “በቀባቸው” ሰዎች አማካኝነት ሕዝቡን እንደሚያድን የሚናገር በመሆኑ ነው። በአማርኛው “የተቀባ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል በዕብራይስጥ “መሲሕ” በግሪክኛው ደግሞ “ክርስቶስ” የሚል ትርጉም አለው። ሐና ስለ ክርስቶስ መምጣት ትንቢት ተናግራለች! የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያድነው እርሱ ነውና። በመንፈስ ቅዱስ ከፀነሰች በኋላ የማሪያም

የምስጋና ቃል በ 1 **ሳሙኤል 2፡1–10** ካለው ከሐና ቃል ጋር የተያያዘ ነው ደግሞም (**ሉቃስ 1፡46–55** ይመልከቱ)። ይህ የሚያሳየው በ 1 ሳሙኤል ምዕራፍ 2 ላይ በሐና እየተነገረ የነበረው ስለ ኢየሱስ ነው።

ከሐና ግጥም በኋላ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ስለነበሩት ክፉ ነገሮች የሚገልጹ በርካታ ምዕራፎች አሉ። ከዚያም መጽሐፉ የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ባዕድ አገር የተወሰደበትን ሁኔታ ይናገራል (**1 ሳሙኤል 5–6**)። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደተወ በጊዜው በእሥራኤል ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች የተገለጠ መሆን አለበት። በወቅቱ ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ሕዝብ እየመራ ቢሆንም እንኳ ሕዝቡ ግን ንጉሥ ይፈልግ ነበር። ይህ ደግሞ ሳሙኤልን አስከፋው። ደግሞም ሕዝቡ ንጉሥን የፈለጉት እግዚአብሔርን በታማኝነት ለመከተል ፈልገው ሳይሆን እንደሌሎቹም ሕዝቦች ለመሆን ስለፈለጉ ብቻ ነው (**1 ሳሙኤል 8፡5** ይመልከቱ)። ይህ እንግዲህ እግዚአብሔርን እንደ ንጉሣቸው አለመቀበላቸው የሚያመለክት ነበር ማለት ነው (**1 ሳሙኤል 8፡7** ይመልከቱ)።

አንድ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራቱ ስህተት እንዳልሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ሙሴም ቢሆን ንጉሥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊመራ እንደሚችል ተናግሮ ነበርና (**ዘዳግም 17፡14–20** ይመልከቱ)። በዘዳግም ውስጥ ያሉትን የሙሴ ቃላት በግልጽ እንደሚያሳዩት ይህ ንጉሥ እግዚአብሔር የሚከተል መሆን ነበረበት። የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ መውደድ እና ሕዝቡንም በታዛዥነት መምራት ነበረበት። ነገር ግን በሳሙኤል ዘመን የነበሩቱ ሰዎች ይህን የመሰለ ንጉሥ አይጠይቁም ነበር። የእግዚአብሔርንም መልክና አምሳል የሚያንጸባርቅ ንጉሥ አይፈልጉም ነበር (**ዘፍጥረት 1፡26–28** ይመልከቱ)። ይልቁንም ልክ እንደ ሌሎችም ሕዝቦች የምድር ነገሥታትን መልክ የሚያንጸባርቅ ንጉሥ ፈለጉ! እግዚአብሔርም የሰጣቸው ይህንኑ ነው። ንጉሥ ሳኦል እንደሌሎች ሕዝቦች ነገሥታት ነበርና። ሳኦል በጣም ረጅም ከመሆኑ የተነሳ እውነትም ንጉሥ ይመስል ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን በሙሉ ሃይሉ አይወድም ነበር፤ የእግዚአብሔርንም ቃል አያከብርም ነበር። 1 ሳሙኤል የንጉሥ ሳኦል ዘመን ይተነትናል። ደግሞ ሳኦል የእግዝሐብሔርንም ሕዝብ ወደ ታዛዥነት አልመራም።

ምንም እንኳን ሳኦል ለእግዚአብሔር ታማኝ ባይሆንም እንኳን እግዚአብሔር ግን የእሥራኤል ሕዝብ አድኖዋቸዋል። ይህም የእግዚአብሔርን ምሕረትና ታማኝነቱን ከማሳየቱም በላይ በሲና ተራራ ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር የገባው የቃል ኪዳን ክፍል መጠበቁን ያስገነዝበናል።

በ 1 ሳሙኤል 15 ላይ እግዚአብብሔር ሳኦልን በእሥራኤል ላይ በንጉሥነቱ መቀጠል እንደሌለበት ደነገገ። በዚሁ መሠረት በ 1 ሳሙኤል 16 ላይ ሌላ ሰው በእሥራኤል ላይ ንጉሥ እንዲሆን ተቀባ። ይህም ሰው ዳዊት ይባላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ዳዊት በጣም አስፈላጊ ሰው ነው። በ 1 ሳሙኤል ምዕራፍ 16 ምንም እንኳን በእሥራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ የተቀባ ቢሆንም በ 2 ሳሙኤል እስከተገለጸው ጊዜ

ድረስ በእሥራኤል ላይ መግዛት አልጀመረም ነበር። በ 1 ሳሙኤል 16 እና 2 ሳሙኤል መካከል ዳዊት በእግዚአብሔርና እና በጥቂት የእሥራኤል ሰዎች ዘንድ ንጉሥ እንደሆነ ታውቆ ነበር፤ ነገር ግን አብዛኛው የእሥራኤል ሕዝብ አሁንም ሳኦል ንጉሥ እንደሆነ ይቆጠር ነበር። ይህም ከጌታ ኢየሱስ ጋር ይመሳሰላል። በምድር ላይ እያለ በነቢይ ተቀባ። ይህም መቀባት የተከናወነው በኢየሱስ ጥምቀት ጊዜ ነበር። ኢየሱስ በተጠመቀበት ወቅት እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ "ልጁ" እንደሆነ ከሰማይ ተናግሯል። ይህም እግዚአብሔር ኢየሱስ የተቀባ ንጉሥ መሆኑን እያወጀ ነበር! ነገር ግን ሰዎች ኢየሱስን እንደ ንጉሥ አያውቁቱም ነበር። ልክ እንደ ዳዊትም ኢየሱስ ስደት ደርሶበታል እንደዚሁም ደግሞ አብዛኛው ሕዝብም ሌላውን ሰው (ቄሳርን) ማለት ነው እንደ ንጉሣቸው ይቆጥሩ ነበር። ይሁን እንጂ ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን እንደ ንጉሥ የሚቆጥሩበት ዘመን ይመጣልና። በዚህ መንገድ የዳዊት መንግሥት ከክርስቶስ መንግሥት ጋር ተመሳሳይ ነው። ዳዊት የክርስቶስ **ምሳሌ** ነው። ይህም ማለት በብዙ መልኩ ዳዊት ኢየሱስን ይመስላል ማለት ነው።


ዳዊት በጎልያድ ላይ የተቀዳጀው ድል ዳዊት ሌላው ክርስቶስን የሚመስልበት መንገድ ነው (1 ሳሙኤል 17 ይመልከቱ)። ጎልያድ በወቅቱ የእግዚአብብሔር ሕዝብ ሊያሸንፈው የማይችለው ጠላት ነበር። ነገር ግን ዳዊት ወደ ፍልስጤማውያን ሰፈር ሄዶ ይህን ጠላት ድል አደረገ። ዳዊት ጎልያድን ድል ካደረገ በኋላ ሕዝቡ ዳዊትን ተከትሎ ወደ ጦርነት ገባ። እንደዚሁም በተመሳሳይ መልኩ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊያሸንፈው የማይችለውን ጠላት አሸነፈ። ኢየሱስ በመስቀል ሞቱ ሰይጣንን፣ ሞትን እና ኃጢአትን አሸንፏል። ዳዊት ጎልያድን ድል ካደረገም በኋላ ጦርነቱ እንደቀጠለ ሁሉ ዛሬም ጦርነት እየተካሄደ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ኢየሱስን ተከትሎ በውጊያው ተቀላቅለዋልና። እንደዚሁም ሌሎችም በዳዊት ንግሥና ውስጥ የሚታዩ አንዳንድ ነገሮች የክርስቶስ የግዛት ዘመን ምሳሌዎች ናቸው። ለምሳሌ ዳዊት ብዙ መዝሙሮችን ጽፏል፣ የእሥራኤልንም አምልኮ መርቷል። ጠበበኛ ሰባኪ ወይም አስተማሪ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ዳዊትን እንደ ዋና ጀግና በመቁጠር እርሱ ላይ አያተኩርም። ይልቁንም ሰባኪው ወይም አስተማሪው ዳዊትን በመጠቀም ከክርስቶስ ጋር ያወዳድራል ወይም ያነጻጽራል።


የመጽሐፈ ሳሙኤል ጸሐፊ፤ አንባቢ ዳዊትን እንደ ፍፁም ንጉሥ አድርጎ እንዲያየው እንደማይፈግ ግልጽ ነው። ድራሲው ስለ ዳዊት ኃጢአት በግልጽ ተናግሯልና (2 ሳሙኤል 11 እና 24 ይመልከቱ)። በዚህ መንገድ ዳዊት እንደ ክርስቶስ አይደለም።

**2 ሳሙኤል 7፡1–17** እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። እነዚህ ጥቅሶች ደግሞ በተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ተጠቅሰዋል። 2 ሳሙኤል 7 **እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን** ይገልጻል። ይህም አንዳንድ ጊዜ **የዳዊት ኪዳን** በመባል ይታወቃል። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ እግዚአብሔር ለዳዊት የተናገረውን እነመለከታለን። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ለዳዊት የተናገረው ቢሆንም ቃሎች ግን

በሰዎች ሁሉ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ናቸው። እግዚአብሔር ለዳዊት እንዲህ አለው፡- “ዕድሜህም በተፈጸመ ጊዜ ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ ከወገብህ የሚወጣውን **ዘርህን** ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ **መንግሥቱንም** አጸናለሁ። እርሱ ለስሜ **ቤት** ይሠራል የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ። እኔም አባት እሆነዋለሁ እርሱም **ልጅ** ይሆነኛል።” ይህ ኢየሱስ የእግዚአብሔር የዘላለም ንጉሥ እንደሆነ የሚያመለክት ነው! ኢየሱስ የዳዊት **ዘር** ነው። ለዚህም ነው በአዲስ ኪዳን ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስን “የዳዊት ልጅ” ብለው የሚጥሩት (ለምሳሌ **ማቴዎስ 9፡27፣ 12፡23፣ 15፡22፣ 20:30–31፣ 21፡9፣ 21፡15 እና 22፡42** ይመልከቱ)። ይህ የተስፋ ቃል የዳዊት ልጅ ዘላለማዊ መንግሥት ይኖረዋል፣ እግዚአብሔር የሚመለከበትን ሥፍራ (መቅደስ) ይሠራል፣ እንደዚሁም ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ልጅ ልዩ ግኑኝነት ይኖረዋል ማለት ነው። እነዚህን ሁሉ ተስፋዎች የሚፈጽም ኢየሱስ ነው! ይህም ደግሞ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሷል። ለምሳሌ ያህል ኢየሱስ በተጠመቀበት ወቅትና ኢየሱስ በተራራ ላይ ሳለ **በተለወጠም ጊዜ “ይህ ልጄ ነው!” የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ። እንግዲህ 2 ሳሙኤል 7 ን የተፈጸመው በኢየሱስ መሆኑን እግዚአብሔር ለሰዎች እየተናገረ ነበር። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው!** ይህ የሳሙኤል ክፍል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተጠቅሷል። እንደዚሁም ደግሞ በሌሎችም መጽሐፎች በነቢያት እና በድርሳናት ውስጥ ተጠቅሰዋል። እነዚህ ጥቅሶች የሚነገሩት ስለ ኢየሱስ መሆኑን የመምህሩ ወይም የሰባኪው መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው! የእግዚአብሔርም ልጅ መጣ ቤተ መቅደሱንም (ቤተ ክርስቲያንን!) ሠራ። ለዘላለምም በዙፋኑ ላይ ይቀመጣል!

2 ሳሙኤል የዳዊትን የግዛት ዘመን ፍጻሜ በመናገር ያበቃል። በዳዊት የንግሥና ዘመን ብዙ ችግሮች ነበሩ። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ በዳዊት ኃጢአት ምክንያት የተከሰቱ ነበሩ። ስለዚህ አንባቢው ዳዊትን እንደ ማንኛውም ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን መገንዘቡ አስፍላጊ ነገር ነው፤ ይህም አንባቢው ከዳዊ ይልቅ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ጀግና እንዲመለከት ይረዳዋልና። ዳዊት ልክ እንደሌላውም የሰው ዘር አዳኝ ያስፈልገው ነበር። እርሱም እንደ ሌሎችም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የክርስቶስን መምጣት ተስፋ ያደርግ ነበርና።




MAR MEDITERRÁNEANO
ISRAEL
JUDÁ

## 7. መጽሐፈ ነገሥት – ከምርኮ በፊት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የገዙት ነገሥታት ታሪክ

ግጥሞች የሳሙኤል ጉልህ ክፍል ሲሆኑ፤ በመጽሐፉ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ ስላላቸው ስልታዊ አቀማመጥ ትኩረት የሚጠይቅ ቢሆንም በነገሥታት ዘንድ ግን ጎልተው የሚታዩ አይደሉም። በ **2 ነገሥት 19፡20–28** ላይ አንድ ግጥም አለ። እንደገና ሰባኪዎች እና አስተማሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ዓይነት ጽሑፎች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ እና እንዲረዱ አስፈላጊ ነው።

የ 1–2 ነገሥት ደራሲ (ወይም ደራሲዎች) አይታወቅም። 1–2 ነገሥት በመጀመሪያ በዕብራይስጡ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበር። ስለዚህ 1–2 ነገሥት እንደ አንድ መጽሐፍ ማለትም የነገሥታት መጽሐፍ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ነገሥት ከነቢያት ውስጥ አራተኛው መጽሐፍ ነው። በነቢትያትም ውስጥ በመጀመሪያ የመጻሕፍት ምድብ ውስጥ ይገኛል። እንደገና ለማስታውስ ያህል በነቢያት ውስጥ ሁለት ዓይነት መጻሕፍት አሉ፦ የታሪክ መጻሕፍት (ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሳሙኤል እና ነገሥት) እንደዚሁም የማብራሪያ መጻሕፍት (ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ እና አሥራ ሁለቱ) ናቸው።

ነገር ግን ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍት ቢሆንም በነቢያት ማብራሪያ ምድብ ውስጥ ከብዙ መጻሕፍት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ኢሳይያስ፣ኤርሚያይስ፣ሆሴዕ፣አሞጽ፣ዮናስ፣ሚኪያስ፣ናሆም፣ ዕንባቆም እና ሶፎኒያስ የተጻፉት በነገሥታት ውስጥ በተገለጸው ጊዜ ነው። በዚህ ምክንያት ነገሥታት በልዩ ሁኔታ በነቢያት ከተጻፉት የማብራሪያ መጽሐፍት ጋር የተቆራኙ ናቸው። ነገሥታት ለነቢያት አንባቢዎች አስፈላጊ የጀርባ መረጃ ይሰጣሉ። (ምናልባት ኢዩኤል የተጻፈው በነገሥታት ውስጥ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ደግሞም ሕዝቅኤል፣ አብድዩ፣ ሐጌ፣ ዘካሪያስ እና ሚልክያስ የተጻፉት በነገሥታት ውስጥ ከተገለጸው ጊዜ በኋላ ነው።)

መጽሐፈ ሳሙኤል ሲጨርስ መጽሐፍ ነገሥት ደግሞ ይጀመራል። መጽሐፈ ነገሥት የሚጀምረው በዳዊት የግዛት ዘመን የመጨረሻ ቀናት እና የልጁ የሰለሞን ደግሞ የግዛት ዘመን መጀምሪያ በመናገር ነው። መጀመሪያ ላይ ሰለሞን በ **2 ሳሙኤል 7፡1–17** ቃል የተገባው "የዘላለም" ንጉሥ ይመስላል። ሰለሞን ከእግዚአብሔር ታላቅ ጥበብ የተሰጠው፣ እግዚአብሔርንም የሚወድ ቤተ መቅደሱንም ደግሞ የሠራ ንጉሥ ነው። ደግሞም እሥራኤልን ወደ ወርቃማ ዘመን መርቷል (1 ነገሥት 1–10 ይመልከቱ)። ሰለሞን በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ **የክርስቶስ** ምሳሌ ነበር። ይህ ማለት የሰለሞን ንግሥና የኢያሱስ ክርስቶስ የመግዛት ዘመን ሥዕላዊ መግለጫ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ ጥበበኛ ሰባኪ ወይም አስተማሪ ስለክርስቶስ ዘላለማዊ መግዛት ለመናገር የሰለሞንን የመጀመሪያ ዓመታት ይጠቀማል።

ይሁን እንጂ ሰለሞን የነገሠባቸው የኋለኞቹ ዓመታት እንደ ክርስቶስ መንግሥት አይደለም። ሰለሞን ከእግዚአብሔር ተመልሶ ሌሎችን አማልክት ማምለክ ጀመረ። በ **ዘዳግም 17፡14–20** በሙሴ የተሰጡትን ነገሥታትን የሚመለከቱ ሕጎችን ሁሉ ጥሷል። ለምሳሌ ያህል ብዙ ፈረሶችን ሰበሰበ፣ ብዙ ሴቶችን አገባ፣ ለርሱም ብዙ ብርና ወርቅ አከማቸ።

በሰለሞን አለመታዘዝ ምክንያት አንድ የነበረው የእሥራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፈለ – ይሁዳ በደቡብ በኩል እንደዚሁም በሰሜን ደግሞ አሥሩ የእሥራኤል ነገድ የየራሳቸው መንግሥት አደረጉ (**1 ነገሥት 12፡16–24** ይመልከቱ)። ከንጉሥ ዳዊት ጋር የሚዛምዱት ነገሥታት በይሁዳ ነገሡ። ከንጉሥ ዳዊት ጋር ዝምድና የሌላቸው ነገሥታት ደግሞ በእሥራኤል ላይ ይገዙ ነበር። ከመጀመሪያው ጊዜ አንስቶ የሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥት በታላቅ የጣዖት አምልኮት ጥፋተኛ ነበር። የመጀመሪያው የእሥራኤል ንጉሥ በእሥራኤል ውስጥ ሁለት የወርቅ ጥጃዎችን አሠርቶ አኖረ (**1 ነገሥት 12፡25–33** ይመልከቱ)። ሕዝቡ ወደ ደቡቡ መንግሥት ወደ ይሁዳ ቤተ መቅደስ ሄደው እንዲያመልኩ አልፈለገም ነበር። ስለዚህ የእሥራኤል ሕዝብ ንጉሳቸው ያዘጋጀውን የወርቅ ጥጃዎችን ማምለክ ጀመሩ። በእሥራኤል (በሰሜኑ) ከነበሩት ነገሥታት አንዳቸውም እንኳን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው ያመለኩ አልነበሩም። ሁሉም በአንድም በሌላ መልኩ ጣዖትን ማምለክ ችለዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ አንዳንድ የይሁዳም ነገሥታት ደግሞ የጣዖት አምልኮትን ይለማመዱ ነበር። በእርግጥ አንዳንዶች እግዚአብሔርን በመታዘዝ ለመራመድ ሞክረዋል። ይሁን እንጂ ታዛዥ ከነበሩቱ ነገሥታት ታዛዥነታቸው በከፊል ብቻ ነበር። እንደዚሁም ይሁዳም ቢሆን እንደ እሥራኤል በቀጥታ የጣዖት አምልኮን ሙሉ በሙሉ ባይቀበልም፤ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ በመጓዙ ጥፋተኛ ነበር።

የነገሥታት መጽሐፍ በእሥራኤል ውስጥ ስለተፈጸሙት ክንውኖችና በይሁዳ ስለተፈጸሙት ክንውኖች በሚገልጹ ታሪኮች መካከል የሚፈራረቅ ነው። መጽሐፈ ነገሥት በዋንኛነት በእሥራኤልና በይሁዳ በሚነግሡት ነገሥታት ላይ ትልቅ ትኩረት የሚያደርግ ቢሆንም መጽሐፉ ደግሞ በእሥራኤል ውስጥ ድንቅ ተአምራትን ይሠሩ በነበሩት ነቢያትም ላይ የሚያተኩር ነው። በተለይም በሁለት ነቢያት ላይ ትኩረት ያደርጋል – ይህም በኤልያስና በኤልሳዕ ላይ ነው። ነገሥታት የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆኑ ሁሉ ነቢያትም የክርስቶስ ምሳሌ ናቸው። ተአምራቶቻቸው ኢየሱስ በሕዝብ መካከል ያከናወነውን ሥራ የሚያሳዩ ትናንሽ ሥዕሎች ነበሩ።

ኢየሱስ የመጨረሻው ንጉሥና ደግሞም የመጨረሻውም ነቢይ ነው። (እርሱም ሊቀ ካህን ነው፤ ይሁን እንጂ ካህናት በነገሥታት ውስጥ ዋና ትኩረት አልነበሩም።

መጽሐፈ ነገሥት የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ለመከተል ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ንጉሥ እንደ ሚያስፈልግ ያመለክታል። መጽሐፉ ከእሥራኤልም ነገሥታት ይሁን ወይም ከይሁዳ ነገሥታት መካከል አንዳቸውም (ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውንም ጫምሮ ማለት ነው) የሕዝቡን ልብ ሊለውጡ እንዳልቻሉ ያሳያል። ስለዚህ መጽሐፉ የተሻለ ንጉሥ እንዲመጣ በመመኘት ጥማትን የሚፈጠር ነው። ምንም እንኳን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ነገሥታት ቢኖሩም እነዚህ ነገሥታት ግን ሁሉም አንዳይነት ችግር አለባቸው ያም ሞት ነው። ስለዚህ መጽሐፈ ነገሥት ለዘላለም የሚነግሥና የማይሞት ንጉሥ እንዲመጣ ረሃብን ይፈጥራል።



## 8. የነቢያት ጠቃሚ ቃል እና ተግባር

የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ በይሁዳና በእሥራኤል በነበሩት **ነገሥታት** ድርጊትና መታዘዝ ወይም አለመታዘዝ እንዲሁም በይሁዳና በእሥራኤል ውስጥ በነበርው **በሕዝቡ** ድርጊትና መታዘዝ ወይም አለመታዘዝ ላይ ያተኩራል። ነገር ግን በመጽሐፈ ነገሥት ወስጥ መጽሐፉ የሚያተኩርባቸው ሌላ የሰዎች ቡድን አለ። ደራሲው በዚህ ጊዜ ውስጥ በተነግሩት ቃላቶች እና ድርጊቶች ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል። በምጽሐፈ ነገሥት ውስጥ ከነበሩት **ነቢያት** መካከል አንዳንዶቹ እንዳውም አልተጠቀሱም። አንዳዶቹ ደግሞ ተጠቅሰዋል። ይሁን እንጂ የመጽሐፈ ነገሥት ፀሐፊ በዋንኛነት ለሁለት ነቢያት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡- ለኤልያስና ለኤልሳዕ።

አስታውሱ በነቢያት ውስጥ ሁለት የመጽሐፍ ምድቦች አሉ። ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሳሙኤል እና መጽሐፈ ነገሥት እነዚህ የታሪክ መጽሐፍት ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት የእሥራኤል ሕዝብ ታሪክ ከኢያሱ ዘመን አንስቶ ለሁለት (እሥራኤልና ይሁዳ) በመባል እስከተከፈለበት ጊዜ ድረስ እንደዚሁም ደግሞ ይሁዳ በባቢሎን እጅ ወድቆ በግዞት እስከ ተወሰደበት ጊዜ ድረስ ያለውን ታሪክ ይዘግባሉ። ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ እና አሥራ ሁለቱ ደግሞ የማብራሪያ መጻሕፍት ናቸው።


በነቢያት ውስጥ ያሉትን መጽሐፎች በሁለት ሊከፈሉ እንደሚችሉ ሁሉ በነዚያም በነቢያት ውስጥ ያሉት ነቢያት ደግሞ በሁለት ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ። በመጀመሪያ የመጽሐፍት ምድብ ውስጥ ያሉ ነቢያት (ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሳሙኤል፣ መጽሐፈ ነገሥት) በይበልጥ የሚታወቁት **በሥራቸው** ነው። ይህም ተስማሚ አቀራርብ ነው፤ምክንያቱም የመጀመሪያው በነቢያት ውስጥ ያሉትን የመጽሐፍት ምድብ ስለ እሥራኤል ታሪክ (ወይም ድርጊት) ላይ ነው የሚያተኩሩት። ነገር ግን በነቢያት ውስጥ በሁለተኛው የመጽሕፍት ምድብ ውስጥ ያሉት ነቢያት በይበልጥ የሚታወቁት **ቢቃላቸው** (በመልዕክታቸው) ነው። ይህም ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም በነቢያት ውስጥ ያሉት ሁለተኛው የምጻሕፍት ምድብ በዚህ ጊዜ ወደ እሥራኤል ስለተነገሩት የነቢያት ቃል ወይም መልዕክት ነው።


በዚህ የነቢያት መጽሐፍ የመጀመሪያ ምድብ ውስጥ ያለው ጸሐፊ በነቢያት ሥራ ላይ ያተኩራል ምክንያቱም በዚህ ጊዜ ውስጥ ነቢያት ያከናወኗቸው ተግባራት የእግዚአብሔርን ኃይል በግልጽ የሚያሳዩ ነበሩና። እግዚአብሔር እውን መሆኑንና ሕዝቡ ከጣዖት አምልኮ ንስሐ መግባት እንዳለባቸው ለማሳየት ታስቦ የተከናወኑ ነበርና።

ከዚህ ውጪ የነቢያት ተግባር ባአል (የባአል አምልኮት) ውሸት መሆኑን ለማሳየት ነበር። በተጨማሪም የነቢያቱ ተግባር በባአል ማንነት እና ሃይል ላይ ማላገጥ ወይም ማሾፍም ነበር። ይህ በነቢያቱ በሌሎች አማልክቶች ላይ በዓላማ በቅኔያዊ ንግግር መቀለድ አንዳንዴ በእንግሊዝኛው **ፖለሚካል ነገረ መለኮት**

ይባላል። ለምሳሌ ያህል በእሥራኤላውያን ባአልን ማምለካቸው ምድሪቱን በጣም ፍሬያማ እንድትሆን ያስችላታል ብለው ያስቡ ስለነበር፤ በኤልያስ ዘመን የነበረው የሦስት ዓመት ተኩል ረሃብ በባአል ላይ ለማሾፍ ታስቦ የተካሄደ ነበር። የባአል ሐውልቶች ብዙን ጊዜ በእጃቸው የመብረቅ ብልጭታ ይይዛሉ። ይህም ባአል የዝናብ አምላክ እንደ ሆነ ይቆጠር እንደነበር ያሳያል። በኤልያስ ቃል መሠረት መዝነብ አቁሟል (**1 ነገሥት 17፡1**) እና ደግሞ ኤልያስ እስኪጸልይ ድረስ እንደገና አልዘነበም (**1 ነገሥት 18፡41–46** ይመልከቱ) የዝናቡ መዝነብ አለመቻል ባአል መሳለቂያ እንዲሆን ታስቦ የተደረገ ነበር። በአየሩም ላይ አምላክ ነው ይሉት የነበረው ባአል ዝናብን ግን ሊያዘንብ አልቻለም! ስለ ባአል በጥንታዊ ታሪኮች ውስጥ እንደተጻፈው ከሆነ፤ ባአል በሰማይ በሠረገላ ሲጋልብ ይታያል። ስለዚህ ኤልያስ ከአክዓብ ሠረገላ ፊት ለፊት መሮጡ የእግዚአብሔር ነቢያት በእግራቸው የሚሮጡ በሠረገላው ውስጥ ከሚገኘው ከባአል የበለጠ ፈጣን መሆናቸውን የሚያሳይ ነበር! ይህ ደግሞ በባአል ላይ መሳለቂያ ነበር። ይህ አወዛጋቢ ነገር መለኮት ዓላማው ለእግዚአብሔር ሕዘብ መልዕክት ለማስተላለፍ የታቀደ ነበር። ሕዝቡ የተጠራው ከኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡና ወደ ሕያው እግዚአብሔር እንዲመለሱ ነበርና።

በ **ዘዳግም 18፡20–22** ውስጥ እሥራኤላውያን እውነተኛና ሐሰተኛ ነቢያት እንዴት ለይተው ማወቅ እንዳለባቸው ጠቃሚ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል። ሐሰተኛ ነቢያትን በተቀበሉት መሠረት እግዚአብሔር ስለ ሐሰተኛ ነቢያት በተመለከተ የተናገረውን ቃል እንዳልታዘዙ ግልጽ ነው።







## 9. በነቢያት የተደረጉት ተአምራቶች አንባቢያንን ለክርስቶስ ተአምራት ያዘጋጃሉ

በብዙ የብሉይ ኪዳን መጻሐፍት በእግዚአብሔር ነቢያት ተአምራት ተፈጽመዋል። የመጽሐፈ ነገሥት አንባቢ ደግሞ በተለይም በእሥራኤልና በይሁዳ ነቢያት ስለተደረጉት በዙ ተአማራት ያነባል። በነቢያት የሚደረጉ ተአምራቶች በጥንቃቄ ሊታሰበበት ይገባል። ተአምራቶቹ የእግዚአብሔር ኃይልና እግዚአብሔርም ደግሞ በነገር ሁሉ ላይ (ክፉ ነገሥትታንና ተፈትሮንም ጨምሮ) ማለት ነው፤ የበላይ እነደሆነና የሚፈልገውንም ሁሉ ማድረግ እንደሚችል የሚያሳዩ ማስረጃዎች ናቸውና። እደዚሁም ደግሞ ትልቅ ክፉት በነገሠበት ዘመን እንኳን ቢሆን እግዚአብሔር በሰማይ እየገዛ እንዳለ የሚያሳዩ ማስረጃዎች ናቸው። እግዚአብሔር አሁንም በኃጢአት ላይ እየፈረደ ይገኛል። በተጨማሪም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚያስብ የሚያሳይ ማስረጃ የሚያቀርቡ ናቸው። ተአማራቶች ግን የብሉይ ኪዳን ታሪኮች ብቻ አይደሉም። በአዲስ ኪዳን ከተደረጉ ተአምራቶች ጋርም መያያዝ አለባቸው። በተለይም አስተዋይ ሰባኪ ወይም አስተማሪ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ተአምራት ኢየሱስ ካደረጋቸው ተአምራት ጋር ያያይዛቸዋል። ይህ አስፈላጊ ነገር ነው፤ ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን ነቢያት የክርስቶስ **ምሳሌዎች** ናቸውና። ማለትም ተአምራቶቹ በሆነ መንገድ የክርስቶስን ተአምራቶች እና አገልግሎቱን ለመሳል የታሰቡ ናቸው። ለምሳሌ ኤልያስ የሞተን ልጅ ማስነሳቱ (1 ነገሥት 17፡17–24 ይመልከቱ) ስለክርስቶስ ለሚያነብ ሰው ክርስቶስም ሙታንን እንደሚያስነሳ ለማስታውስ ነው። ይሁን እንጂ ክርስቶስ ግን አንድን ሰው ብቻ አያስነሳም። ይልቅስ በእርሱ የሆኑትን ሁሉ ያስነሳል! ኤልያስ በሰራፕታ ለነበረችው መበለት ምግቡ እንዲበዛ ባደረገ ጊዜ (የሐዋሪያት ሥራ 17፡8–16 ይመልከቱ)፤ ይህ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ሕዘብ ፍላጎት ለዘላለም የሚያሟላ መሆኑን ምሳሌ ነው! ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ ነውና (ዮሐንስ 6፡22–59)።

ኢየሱስ ነቢይ እንደሆነ ተናግሯል (ማቴዎስ 13፡57 ይመልከቱ)። እግዲህ ከላይ ከተዘረዘረው በተጨማሪ የክርስቶስ ተአምራት እሱ ኢየሱስ ነቢይ መሆኑንም ያስረግጣል። እንደ ብሉይ ኪዳንም ነቢያት ተአምራትን አድርጓልና። በኢየሱስ ዘምን የነበሩት ሰዎችም ኢየሱስ ነቢይ መሆኑን ተገንዝበው ነበር። ለዚህም ነው ብዙዎች "ነቢይ ነው" ያሉት (ማቴዎስ 16፡14፣ 21፡11፣ ማርቆስ 6፡15 እና 8፡28 ይመልከቱ)። ኢየሱስ ግን እንዲያው ነቢይ ብቻ አይደለም። አገልግሎቱም ቢሆን "ነቢይ" መሆኑን ያሳያል። ነገር ግን ኢየሱስ በዘዳግም 18፡15–19 ሙሴ የተናገረለት ይመጣል የተባለው ነቢይ ነው (በተጨማሪም የሐዋሪያት ሥራ 3፡17–26 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ነቢይ ብሎ ያስነሳው ስለሆነ ሁሉንም ሰዎች እሱን እንዲሰሙና እሱንም መታዘዝ እንዲችሉ ታዝዘዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱሱ ተራራ በተለወጠ ጊዜ እግዚአብሔር ለደቀመዛሙርቱ የተናገራቸውን ቃላት ይመልከቱ "ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው ከደመናውም፡- የምወደው ልጄ ይህ ነው **እርሱን ስሙት** የሚል ድምፅ መጣ" (ማርቆስ 9፡7)። እነዚህ ቃላት ልጁን ስለመስማት

በዘዳግም 18 ላይ “ነቢዩን” ስለመስማት ከተነገሩ ቃላት ጋር የሚዛመዱ ናቸው። እነዚህ ቃላት ኢየሱስ እግዚአብሔር ለመጨረሻ የሚናገርው በእርሱ እንደሆነ ያሳያሉ። የእሥራኤል ሕዝብ ወደ እነርሱ የተላኩትን ነቢያት ይሰሙ እንደ ነበር ሁሉ ሰዎች ሁሉ የክርስቶስ ቃል መስማት ይኖርባቸዋል። የኢየሱስ ተአምራቶች ምልክት እንደነበሩ ለመረዳት ዮሐንስ 20፡30–31 ይመልከቱ። ወደ ታላቅ ነገር ለማመልከት የታቀዱ እንደ ምድራዊ ምልክቶች ነበሩና። በተለይም የኢየሱስ ተአምራት ኃይሉን፣ ታላቅነቱን እና የእግዚአብሔርን ምሕረት የሚያመለከቱ ምልክቶች ናቸው።






## 10. በሁለተኛው የነቢያት ክፍል ውስጥ ያሉትን መጽሐፍት እንዴት ነው የተደረደሩት?


የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሦስት ቡድን ተደርድረዋል (**ሉቃስ 24፡44** ይመልከቱ)። እነዚህም ቡድኖች ሕግ፣ ነቢያት እና ጽሑፎች ይባላሉ (ጽሑፎቹ አንዳንድ ጊዜ መዝሙረ ዳዊት ይባላል)። በነቢያት ውስጥ ያሉት የመጻሕፍት ቡድን በሁለት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል። በመጀመሪያው ክፍል ያሉትን መጻሕፍት በእሥራኤል ሕዝብ ታሪክ ላይ ያተኩራሉ። በሁለተኛው ምድብ ያሉት መጻሕፍት በዋናነት የታሪክ ምጻሕፍት አይደሉም። ይልቁን የማብራሪያ መጽሐፍት ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ። ምክንያቱም ስለ እሥራኤል ድርጊት አስተያየት የሚሰጡ መጻሕፍት ናቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ እነዚህ መጻሕፍት እንደ የስብከት ስብስቦች ናቸው። በነቢያት “ማብራሪያ” ቡድን ውስጥ የሚገኙት መጻሕፍት ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ እና አሥራ ሁለቱ ናቸው። “አሥራ ሁለቱ” የተባሉት አንዳንዴ 12ቱ ትናንሽ ነቢያት ይባላሉ እነሱም፡- ሆሴዕ፣ ኢዩኤል፣ አሞጽ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ሚኪያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካሪያስ እና ሚልክያስ ናቸው። እነዚህ አጫጭር የማምብራሪያ መጻሕፍት የተለያዩ ቢሆኑም፤ አይሁዶች ግን አንድ መጽሐፍ አድርገው “አሥራ ሁለቱ” በማለት አዋህዶዋቸዋል። ስለዚህም በነቢያት የታሪክ ክፍል (ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሳሙኤል እና መጽሐፈ ነገሥት) አራት መጻሕፍት ሲኖሩ በነቢያት ማብራሪያ ክፍል ደግሞ (ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ እና “አሥራ ሁለቱ”) አራት መጻሕፍት አሉ ማለት ነው።

በነቢያት የታሪክ ክፍል ውስጥ ያሉት መጻሕፍት በጊዜ ቅደም ተከተል ሲቀመጡ በነቢያት ማብራሪያ ክፍል ውስጥ ያሉት መጻሕፍት በመጠን ውይም በርዝማኔያቸው ቅደም ተከተል ተቀምጠዋል። ኤርምያስ ረጅሙ መጽሐፍ ነው። ስለዚህ በነቢያት ውስጥ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው። ነገር ግን (በዘመናዊው የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ላይ የተዘረዘረው የመጀምሪያው መጽሐፍ አይደለም)። ሁለተኛው ረጅሙ መጽሐፍ ሕዝቅኤል ነው። ሦስተኛው ረጅሙ መጽሐፍ ኢሳይያስ ነው። ትንሹ መጽሐፍ ደግሞ “አሥራ ሁለቱ” ነው።

አንዳንድ ጊዜ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል እና ኢሳይያስ “ዋንኞቹ” ነቢያት ተብለው ይጠራሉ። ይህ ማለት ግን ከ“ትናንሾቹ” ነቢያት (ማለትም “አሥራ ሁለቱን”) የበለጠ አስፈላጊ ናቸው ለማለት አይደለም። መጽሐፎቹ ከ“ትናንሾቹ” የነቢያት መጻሕፍት በመጠን ይበልጣሉ ማለት ነው። “ትላልቆቹ” ነቢያት እና “ትናንሾቹ” ነቢያት ሁሉም በእግዚአብሔር መንፍስ አነሳሽነት የተጻፉ ናቸውና። ሁሉም እውነት ናቸውና መጠናት አላባቸው።


በነቢያት ማብራሪያ ክፍል ውስጥ ዋናው ርዕስ ጉዳይ በእሥራኤል እና ብይሁዳ ላይ በጣዖት አምልኮት ምክንያት የሚመጣው ፍርድ ነው። ነቢያት እሥራኤልና ይሁዳ ከኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡ ጠርተዋቸው ነበር። ሕዝቡ ግን ከጥቂት ቅሬታዎች በቀር ንስሃ መግባት አልፈለገም። ይልቁንም ነቢያትን አሳደዱ ገደሉዋቸውም (**ማቴዎስ 5፡12፣ 23፡29፣ 23፡34–37** እና **ሉቃስ 11፡47** ይመልከቱ)። ነቢይን መግደል ትልቅ ኃጢአት ነው። ይህም እግዚአብሔርን ዝም ለማሰኘት የተደረገ ሙከራ ነበር።





## ፲. በነቢያት የተነገረው ቃል አንባቢውን ለክርስቶስ ቃል ያዘጋጀዋል

በ "ነቢያት" ውስጥ ያሉት ሁሉም የማብራሪያ መጻሕፍቶች ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ መንገዶቹ እና ስለ እቅዶቹ ማስተማርን ያካትታሉ። በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ያለውን የነቢያት ትምህርት በጥንቃቄ ሊታሰብበት ይገባል። እነዚህ ትምህርቶች በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ በመገንዘብ፤ ትምህርቶቹ ዛሬም ክርስቲያኖች ሊያጠኑትና ሊጠቀሙባቸውም እንደሚገባ ግልጽ ነው። በብሉይ ኪዳን የተደርጉ ተአምራቶች ኢየሱስን እንድናስታውስ የታሰቡ ነበሩ፤ እንደዚሁም ደግሞ የብሉይ ኪዳን ነቢያትም ቃልና ትምህርታቸውንም ቢሆን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድናስታውስ የሚያደርጉን ናቸው። ስለዚህ ብልህ ሰባኪ ወይም አስተማሪ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ቃል ከኢየሱስ ትምህርት ጋር ያዛምዳል። ኢየሱስ በቃልም ሆነ በተግባር የእግዚአብሔር ፍጹም ተወካይ ነውና። እንደዚሁም እሱ በ**ዘዳግም 18፡15–19** የተነገረለት "ነቢይ" ነው (በተጨማሪም **የሐዋሪያት ሥራ 3፡17–26** ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ደግሞ "ነቢይ" ብሎ ስላስነሳው ወይም ስለላከው ሰዎች ሁሉ እሱን እንዲሰሙትና ቃሉን እንዲታዘዙ ታዘዋል።



## 12. እሥራኤል ብዙ አማልክቶችን ታመልክ ነበር

አንድ አምላክ ብቻ ነው ያለው። ስለዚህ ሊመለክ የሚገባው እሱ ብቻ ነው። ይህም እውነት በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ግልጽ ተደርጓል። እግዚአብሔርም ደግሞ “ቀናተኛ አምላክ” መሆኑን ገልጿል (**ዘጸአት 20፡5፣ 34፡14፣ ዘዳግም 4፡24፣ 5፡9፣ 6፡15፣ 32፡21** እና **ኢያሱ 24፡19**)። እግዚአብሔር ሌሎችን አማልክት አይታገስም። እሥራኤል እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልኩ ታዝዘዋል (**ዘጸአት 20፡3–5** ይመልከቱ)። ነገር ግን አልሰማ ብለው ሌሎችን አማልክት የሚያመልኩ ከሆነ ከተስፋይቱ ምድር እንደሚባረሩ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል (ለምሳሌ **ዘዳግም 4፡15–26** እና **ዘዳግም 30፡17–18** ይመልከቱ)። በኢያሱ መሪነት ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገቡ፤ በዚያ ሰፍረው የነበሩትን ሕዝቦች ጣዖት አምላኪዎች ስለነበሩ በምድሪቱ ያሉትን ሕዝቦች ማጥፋት ነበረባቸው። እነዚህ እንዲጠፉ የተወሰነባቸው ሕዝቦች “በኮረብታ ላይና በለመለመ ዛፍ ሁሉ ሥር” ጣዖታትን ያመልኩ ነበር (**ዘዳግም 12፡2** ይመልከቱ)። እነዚህ ሕዝቦች ከእሥራኤላውያን በፊት በምድሪቱ ላይ የነበሩት ሁሉ ማለት ነው፤ በመድሪቱ ውስጥ በሁሉም ቦታ ጣዖታትን ያመልኩ ነበር ማለት ነው። እንደዚሁም ደስ ባላቸው ሥፍራ ሁሉ ለጣዖት አምልኮት መሠውያ ይሠሩ ነበር። ስለዚህ እሥራኤላውያን ወደዛ ምድር ሲገቡ ሌሎችን አማልክት ከሚያመልኩ ሕዝቦች ጋር እንዳይተባብሩ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷዋቸው ነበር። ነገር ግን እሥራኤል እነዚህን ትዛዛት አላከበሩም። ይልቁንም የእሥራኤል ሕዝብ የአሕዛብን አማልክት ያመልኩ ነበር። ደግሞም ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ሕብረት ያደርጉ ነበር። በመሆኑም ሌሎች ሕዝቦች የሚያደርጉትን ነገር ያደርጉና እንደሌሎችም ሕዝቦች ያመልኩ ጀመር። በመጨረሻም እሥራኤልውያን የተገለጹበት መንገድ ሌሎች ሕዝቦችም በተግለጹበት መንገድ ነው! “ከፍ ባለው ኮርብታ ሁሉ ከለመለመውም ዛፍ ሥር ሁሉ በታች” ጣዖታትን ለራሳቸው አቆሙ (**1 ነገሥት 14፡23፤ 2 ነገሥት 16፡4፣ 17፡10፤ ኤርምያስ 2፡20፣ 3፡6፣ 17፡2፤ ሕዝቅኤል 6፡13 እና 2 ዜና 28፡4** ይመልከቱ)! ነቢያትም የእሥራኤልን ሕዝብ ስለ ጣዖት አምልኮ አስጠንቅቀዋል። ንስሐ የማይገቡም ከሆነ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አስጠንቅቀዋቸዋል። ሕዝቡ ግን ንስሐ አልገባም። ይልቁንም ነቢያትን ገደሉ። ለምሳሌ ኤልያስ ሕዝቡ በእርሱ ዘመን ያደረጉትን እንዴት እንደገለጸ (በ **1 ነገሥት 19፡10–14** ይመልከቱ).

በ”ነቢያት” የማብራሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙት አብዛኛዎቹ መለልእክቶች የእሥራኤል ጣዖታትን ማምልክ እና እሥራኤል በጣዖት ማምለክ ምክንያት ስለሚመጣባት ቅጣት የሚነገሩ ናቸው።



## ፲፫. የብሉይ ኪዳን ነቢያት በሲና ተራራ የተደረገውን ቃል ኪዳን ደጋግመው ይጠቅሳሉ


አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስለ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ሲናገሩ ተቀዳሚ ሚናቸው ስለ ወደፊቱ ጊዜ መተንበይ ነው በማለት ነው። ያ የእነርሱ ተግባር አንዱ አካል ሆኖ ሳለ ከዋና ተግባራቸው አንዱ ደግሞ ስላለፈው ሩቅ ጊዜ ነገርንም መናገር ነበር። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ለእሥራኤል ሕዝብ ማሳሰብ ነበር (**ዘጸአት 20–24** ይመልከቱ)። በተለይም ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ እና ኢሥራ ሁለቱ በሕጉ ውስጥ የተጻፉትን ትእዛዛት በተደጋጋሚ በመጥቀስ ያመለክታሉ። ነቢያቱ የእሥራኤልና የይሁዳ ሕዝቦች ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን አስታውሰው የእሥራኤልንና የይሁዳን ሕዝቦች ቃል ኪዳኑን በማፍረስ ወንጀል ወቅሰዋል። በዚህ መልኩ ስንመለከታቸው ነቢያቶች ልክ እንደ ዘመናዊ ፖሊሶች ዓይነት ነበሩ ለማለት ያስችላል። ምክንያቱም የእሥራኤልን ሕዝብ ቃል ኪዳኑን በማፍረስ ወንጀል ይከሱ ነበርና።

የሙሴ መጸሐፍ (ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኁልቁ እና ዘዳግም) የተጻፈው ከነቢያት ዘመን ከሙቶ ዓመታት በፊት ነው። መጽሐፉም በእሥራኤል ዘንድ በሰፊው ይታወቅ ነበር፤ ምክንያቱም የሙሴ መጽሕፍ ከሙሴ ዘመን በኋላ በነበሩት ነቢያት ዘወትር ተጠቅሷል። ነቢያት ሕጉን (የሙሴ መጽሐፍ ሌላ መጠሪያ) አንብበው ተረድተውት አምነውበት እና የእግዚአብሔርም ሕዝብ በውስጡ የተጻፈውን እንዲታዘዙ ጠብቀው እንደነበር ግልጽ ነው።

ነቢያት ሕጉን በመጽሐፋቸው ውስጥ ስልታዊ በሆነ ሁኔታ አካተውታል። ከሕጉ በቀጥታ የተወሰደ ቋንቋ በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ።ነቢያት የሙሴ መጽሐፍ ታሪኮችንና ሰዎችን ያመለክታሉ። በሲና ተራራ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል የተደረገውን ቃል ኪዳን ለሕዝቡ ዘወትር ያሳስቧቸዋል። በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ የተመዘገቡትን ክስተቶች ደግሞ ወደፊት ለሚፈጸሙ ክንውኖች አብነት አድርገው ይጠቀማሉ።

ለምሳሌ ኤርሚያስ፣ ኢሳይያስ፣ እና ሆሴዕ **ስለ ዳግማዊ ዘጸአት ክስተት** በግልጽ ተናግረዋል። የመጀመሪያውን የስደት ቃላት እና ዝርዝሮችን ወስደው ስለሚከሰተው ሁለተኛ የስደት ክስተት በገለፃቸው ተጠቅመውበታል። ነቢያት በሕጉ አጠቃቀም ላይ በመመስረት አንባቢዎቻቸው የሙሴን መጽሐፍ በደንብ

እንዲያውቁ በመፈለግ እንደሚጠብቁ ግልጽ ነው። መጽሐፉንም ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል አድርገው እንደሚቆጥሩትም የተገለጠ ነው። ስለዚህ በሙሴ መጽሐፍና በነቢያት መካከል ስላለው ብዙ ትስስር፣ ሰባኪው ወይም አስተማሪው የሙሴን መጽሐፍ ከነቢያት ጋር ማጥናቱ ትልቅ እገዛ ይሰጠዋል።





## 14. ነቢያት ስለ ክርስቶስ መምጣትና ስለ መንግሥቱ ያውቁ ነበር

ምንም እንኳን ነቢያት ባለፈው ጊዜ ስለተገባው ቃል ኪዳን ደጋግመው ቢያስታውሱም ስለወደፊቱም ይናገሩ ነበር። ሁሉም ነቢያት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ስለ ክርስቶስ መምጣትና ስለ መንግሥቱ ጽፈዋል (**የሐዋሪያት ሥራ 3፡18፣ 24** እና **1 ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ)። ይህም ኢየሱስ ስለ ራሱ ለመናገር የነቢያትን ቃል መጠቀም የፈለገው ለምን እንደሆነ ያብራራል (**ሉቃስ 24፡25–27** እና **44–47** ይመልከቱ)። ነቢያት ሕዝቡ ቃል ኪዳኑን ማፍረሳቸውን ሲናገሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ **አዲስ ቃል ኪዳን** እንደሚያመጣ አስታውቀዋል (**ኤርምያስ 31፡31** እና **ሕዝቅኤል 36፡24–27** ይመልከቱ)። ነቢያት ይህ አዲስ ቃል ኪዳን የሚጸናው በክርስቶስ መምጣት እንደሆነ ያውቁ ነበር። ስለዚህም ነቢያት የክርስቶስን መምጣት በጉጉት ይጠባበቁ ነበር (**ማቴዎስ 13፡17** ይመልከቱ)። ምክንያቱም ነቢያት የእምነት ሰዎች ነበሩና።



## 15. ነቢያት ተቀባይነት አጥተው ነበር

ነቢይ ሆኖ በነቢይነት ማገልገል ቀላል ነገር አልነበረም። የነቢያት መልዕክት በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት አያገኝም ነበርና። ምክንያቱም የነቢያት መዕክቶቻቸው ብዙ ሰዎችን የሚያስቆጣ ስለነበረ ነው።

እስቲ እግዚአብሔር የነቢያትን አገልግሎት በተመለከተ እንዴት እንደገለጸው ይመልከቱ፡-

*ስለዚህ በነቢያት እጅ ቆረጥኳቸው፤*

*በአፌም ቃል ገደልኳቸው፤*


*ፍርዴም እንደ ብርሃን ይወጣል። (**ሆሴዕ 6፡5**)።*


የነቢያቱ ቃል እሥራኤላውያንን እንዲቆርጥ ታስቦ ነበር! ይህ የሆነበትም ምክንያት እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለወደደ እና ንስሐ እንዲገቡም ይፈልግ ስለነበር ነው። ነገር ግን የነቢያትን መልዕክት ከጥቂት ካመኑ ሰዎች በስተቀር አብዛኛው ሰው የነቢያቱን መልዕክት አልተቀበለም አይቀበልምም ነበር። ስለዚህ ነቢያትን አሳደዱ (**ማቴዎስ 5፡ 11–12፣ ማቴዎስ 23፡29–39፤ ማርቆስ 12፡1–2፤ ሉቃስ 11፡47–51፣ 13፡34፤ የሐዋሪያት ሥራ 7፡51–53** እና **ዕብራውያን 11፡32–38** ይመልከቱ)። እግዚአብሔር እንዲሰብኩት ወይም እንዲናገሩት በሰጣቸው መልዕክት ምክንያት ብዙዎች ነቢያት ተገድሏል (ለምሳሌ **1 ነገሥት 19፡14** ይመልከቱ)። ነቢያትን መግደል ትልቅ ኃጢአት ነበር፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ዝም ለማሰኘት የሚደረግ ሙከራ ነበርና። የነቢይ ሥራ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ብቻ መሆን ነበር። ስለዚህ ነቢይን መግደል የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደ “መግደል” ዓይነት ሙከራ ነበር ማለት ነው። ይህ በብሉይ ኪዳን ጊዜ እውነት ነበር፤ እንደዚሁም ኢየሱስ ታላቁ ነቢይ በምድር ላይ ሲያገለግልም የሆነው ይኸው እውነት ነበር።

ይሁን እንጂ ጥቂት ቅሬታዎች ደግሞ የነቢያትን ቃል አምነው ለመልዕክቶቻቸው ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም በብሉ ኪዳን እውነት ነበር። ደግሞም ኢየሱስ በምድር ላይ ሲያገለግልም ይህ እውነት ነበር። ዛሬም ደግሞ እውነት ነው። የእግዚአብሔር የሆነ ሕዝብ የነቢያትን መልዕክት ይሰማና ለመልዕክቶቻቸውም ምላሽ ይሰጣል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ጥቂት ቅሬታዎች እግዚአብሔርን ተከትለው የነቢያትን መልዕክት ይሰሙ ነበር፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ጠርቶዋቸው እንዲከተሉትም ልቦና ስለሰጣቸውና ስላስቻላቸውም ነው (ለምሳሌ **1 ነገሥት 19፡18** ይመልከቱ)። ዛሬም ቢሆን የእግዚአብሔር ቅሬታዎች ነቢያትን ይሰማሉ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እርሱን እንዲከተሉ ስላስቻላቸው ነው (**ዮሐንስ 6፡44** ይመልከቱ)።

ቤተ ክርስቲያን በሐዋሪያትና በነቢያት መሰረት ላይ የታነጸች ናት (**ኤፌሶን 2፡20** ይመልከቱ)። በ**ኤፌሶን 2፡20** ላይ "ሐዋሪያት" የሚለው ቃል በመጀመሪያ የተጠቀሰበት ምክንያት፤ ሐዋሪያት የነቢያትን መልዕክት ለአማኞች በመተርጎም ረገድ ትልቅ ሚና ስለነበራቸው ነው።






## 16. በነቢያት ማብራሪያ መጽሐፍት ውስጥ ያሉት መልዕክቶች ቅደም ተከተል

የትንቢት መጻሕፍት ብዙውን ጊዜ የእሥራኤልን የቀድሞ ኃጢአት በሚገልጹ የውግዘት መልዕክቶች እና ስለ ወደፊቱ ጊዜ በሚሰጡ የተስፋ ትንቢቶች መካከል ይለዋወጣሉ። (አንዳንድ ጊዜም የውግዘቱ መልዕክቶች የሌሎችንም ሕዝቦች ኃጢአት በተመለከተ ነበር)። ርዕስ ጉዳዮችን ሲቀይር ደራሲው አያሳውቅም። ሆኖም አንባቢው በነቢያቱ መልዕክት ላይ ተደጋጋሚ ለውጥ መኖሩን የተለመደ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ ስንመለከታቸው በነቢያት ውስጥ ያሉት የማብራሪያ መጽሐፍት ከትረካ መጽሐፍት እንብዛም ልዩነት የላቸውም።

እንደዚሁም ደግሞ በዕብራይስጥ የትንቢቱ ገጽታ በተደጋጋሚ በአሉታዊና በአዎንታዊ መግለጫዎች መካከል የሚቀያየር መሆኑ ነው። የተወሰኑ የጥቅሶች ቡድን አሉታዊ ነው። እነዚህ አሉታዊ ትቅሶች ደግሞ ውዲያውኑ በቡድን በሆኑ አዎንታዊ ጥቅሶች የሚከተሉ ናቸው። ይህ በአሉታዊና በአዎንታዊ መግለጫዎች ማካከል ያለው ድግግሞሽ ወይም ሁደት በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በትንቢት መጽሐፍት ውስጥ የተለመደ ነው። ለምሳሌ በሆሴ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን ምሳሌ ይመልከቱ (**ሆሴዕ 1፡1–9** አሉታዊ ነው)። ክፍሉ ስለ እሥራኤል ውድመት ወይም ጥፋት የሚናገር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ **ሆሴዕ 1፡10–2፡1** አዎንታዊ ነው። ይህም ስለ እሥራኤል ትንሣኤ የሚናገር ነው። ይህ ትንቢት ወደ ፊት በተፈጸመ ጊዜ በተመረጠው መሪያቸው ሥር ሆነው ስለ እሥራኤል መዳንና ታላቅ መብዛት ይናገራል። ይህ የወንጌል ቃል ኪዳን ነው! በተጨማሪ ይመልከቱ **ሆሴዕ 2፡2–13** አሉታዊ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ **ሆሴዕ 2፡14–23** አዎንታዊ ነው። ይህ ንድፍ በመጽሐፉ ውስጥ እነደዚሁ ይቀጥላል። እንደዚሁም ደግሞ በነብያት ማብራሪያ ክፍል ውስጥ ያሉ ሌሎች መጻሕፍትም ይህንኑ መንገድ ይከተላሉ።

ለምንድነው ሁሉም አሉታዊ ክፍሎች አንድ ላይ እና አዎንታዊ ክሎች ደግሞ ለብቻ አንድ ላይ ያልተቀመጡት? ምናልባትም ይህ በአዎንታዊ እና በአሉታዊ ማካከል ያለው ተደጋጋሚ ለውጥ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ መልዕክቶች – አዎንታዊ እና አሉታዊ – በአዲስ ቃላት ደጋግመው እንዲናግሩት ያስችላቸው ይሆናል። የእግዚአብሔር ሰዎች እነዚህን መልዕክት ደጋግመው መስማት ስለሚያስፈልጋቸው በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን መልዕክቶች መድገም አስፈላጊ ነው። እንደዚሁም ሰባከው ወይም አስተማሪው በጽሑፉ ውስጥ አጽንዖት የተሰጠበት ነገር ላይ ትኩርት ለማድርግ ይጠቅመዋል። በተመሳሳይ መልኩ በጽሑፉ ውስጥ አጽንዖት ያልተሰጣቸው አስቸጋሪ ነገሮችን ለመዝለል ቀላል ነው። ይህ ጥበብ አይደለም። ነገር ግን ብልህ ሰባኪ ወይም አስተማሪ በነቢያት ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ አጽንዖት ይሰጣል።



## 17. ባአል ማነው?

የእሥራኤል ሕዝብ በነቢያት ዘመን ብዙ ዓይነት አማልክቶችን ያመልኩ ነበር። በተደጋጋሚ ከሚጠቀሱት አማልክቶች አንዱ ባአል የሚባል አምላክ ነው። አንዳንድ ጊዜ ባአል በነጠላ (“ባአል”) ተብሎ ተጠቅሷል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በብዙ ቁጥር የባአል አማልክቶችን ያምልኩ እንደ ነበር ተጠቅሷል። ያም ሆነ ይህ የባአል አምልኮ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የሚጻረር ነው።


ባአልን ማምለክ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከሴትኛ አዳሪዎች ጋር የሚዛመድ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ሰዎችን ዓይነት ነገር ያጠቃልላል። እነዚህ ሕገወጥ የፆታ ግኑኝነት የተፈፀሙት እንደ ዋና አማልክት ከምትታየው ከአናት (የተጋባት ሴት አማልክት ማለት ነው) ጋር ተመሳሳይ ነገር በማድረግ ለእነዚህ ድርጊቶች ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ነበር። ስለዚህ ሰዎች በምድር ላይ የሚያደርጉትን የሰው ልጆች የፆታ ግኑኝነት በሰማይ ያሉትን አማልክቶች የፆታ ግኑኝነት እንዲፈጽሙ ያነሳሳቸዋል ብለው ያምኑ ነበር፤ ይህም ደግሞ ተስማሚ የአየር ጸባይ እና የግብርና ብልጽግና ያስገኛል ብለው ያምኑ ስለነበርም ነው።


ስለ ባአል የሚናገሩ ብዙ ቁጥር ያላቸው ጥንታዊ ታሪኮች ተገኝተዋል። አንዳንዶቹ ታሪኮች ባአል ያም ከተባለው የባሕር አምላክ ጋር ስላደረገው ጦርነት የሚናገሩ ናቸው። ሌሎች ደግሞ በበጋ ወቅት ድርቅን ከሚያመጣው ሞት ከተባለው አምላክ ጋር ያደረገውን ጦርነት የሚዘክሩ ታሪኮች ናቸው። በእነዚህ ታሪኮች መሠረት የባአል ዋና ረዳት አናት የተባለችው ሴት አማልክት ናት። አናት ደግሞ ባአል የግብረ ሥጋ ግኑኝነት የፈፀመባት አምላክ ነበረች። ደግሞም አናት የባአል እህትም ሚስቱም ተደርጋ ትወሰድ ነበር።

የእሥራኤልና የይሁዳ ሰዎች ባአልን ብቻ አያመልኩም ነበር። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የባአልን አምልኮት ከእግዚአብሔር “አምልኮ” ጋር ያቀላቅሉ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ የሃይማኖቶች መቀላቀል አንዳንድ ጊዜ በእንግሊዝኛ **ሲንክሪትዝም** በመባል ይታወቃል። በነቢያት በተገለጸው የአምልኮ ዘመን መሠረት እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱ “የተደባለቀ” አምልኮ አይቀበልም ነበር (**ዘጸአት 20፡2–6** ይመልከቱ)። በአንድ ጊዜ በባአልም በእግዚአብሔርም መታመን የማይቻል ነገር ነውና። እግዚአብሔር የእሥራኤል ባል  ሆኖ ሚስቱን ለመመገብና ለመንከባከብ ቃል ግብቶ ነበር። ይህም ደግሞ ከእርሷ

(ማለትም ከእሥራኤል) ጋር የገባው ቃል ኪዳን አካል ነበር። ይሁን እንጂ እሷ እንደ እግዚአብሔር "ሚስት" በእንክብካቤው አላማነችም። በመሆኑም ምግብና መጠጡ ወይም የሚያስፈልጋትን ሁሉ የሚሰጣት ባአል መስሏት ነበርና።

እግዚአብሔር አይለወጥም። ዛሬም ቢሆን "ድብልቅ" አምልኮ አይቀበለም (ለምሳሌ **ማቴዎስ 6፡24** ይመልከቱ)። ሰዎች እግዚአብሔርን ብቻውን ለማምለክ መጠንቀቅ አለባቸው። ምክንያቱም ሌሎች አማልክትን የሚያመልኩትን ሁሉ ይቀጣልና።





## 18. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥም እንዴት ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ትንቢት ብዙ ጊዜ ለአንባቢው በግጥም መልክ ይቀርባል። ይህም በኤርምያስ፣ በሕዝቅኤል፣ በኢሳይያስ እና በአሥራ ሁለቱ ውስጥ እውነት ነው። በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት ጥቂት የትረካ ክፍሎች በስተቀር (ለምሳሌ ኤርምያስ፣ ኢሳይያስ፣ ሆሴዕ እና ዮናስ ሁሉም የትረካ ክፍል አላቸው) አብዛኞቹ ነቢያት መልዕክታቸውን የሚያቀርቡት በግጥም መልክ ነው። ግጥም ደግሞ ለአንባቢ እና ለሰባኪ ወይም ለአስተማሪ ታላቅ ስጦታ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥሞችን እንዴት ማንበብ እንደ ሚቻል መረዳት አስፈላጊ ነገር ነው። በመሆኑም ሰባኪ እንዴት መስበክ እንዳለበት ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጣሚ ምንባቦች መማር አስፈልጊ ነው።

ከትረካ ቀጥሎ (ታሪክን በመናገር ጥቅም ላይ የዋለው የጽሑፍ ዓይነት) ግጥም በብሉይ ኪዳን ውስጥ በጣም የተለመደ የአጻጻፍ ስልት ነው። ኢዮብ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሰቆቃው ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ሆሴዕ፣ ኢዩኤል፣ አሞጽ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ሚክያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ እና ዘካርያስ ሁሉም ጥሩ ግጥሞችን ያካትታሉ። ግጥም በሌሎችም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ተበታትኖ ይገኛል (**ዘጸአት 15፡1–18** ይመልከቱ)። ከዚህ ባሻገር ደግሞ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ብዙዎቹ ግጥሞች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሰዋል (**የሐዋሪያት ሥራ 28፡ 26–27** ይመልከቱ)። ስለዚህ ለሰባኪ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥሞችን ማወቅ፣ መረዳት እና መጠቀምም መቻል አስፈላጊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥሞች የሆኑ ቃላትን እና የቃላት ዘይቤዎችን ስለሚጠቀም አንባቢው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ግጥሞች በቀላሉ ማወቅና መማር ይችላል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ግጥሞች በአብዛኛው በግጥም መልክ ቃላቶችን ቤት እንዲመቱ ተድረጎ የተቀመጡ አይደለም። በአንጻሩ በአብዛኛው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ግጥም **ትይዩ** በመባል በሚታወቀው የግጥም መልክ የተጻፈ ነው። ትይዩነት አንድ መስመር አንድ ነገር የሚናገርበት መዋቅር ሲሆን ከሱ በኋላ ያለው መስመር ወዲያው ሃሳቡን ከመጀምሪያው መስመር ይደግማል፤ እናም የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም ሃሳቡን በተወሰነ መንገድ ያጠናክራል። ይህ ከሁለት የባቡር ሀዲዶች ጋር ማመሳሰል ይቻላል (በእርግጥ ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ባለ ሶስት ወይም ከዚያም በላይ መግለጫዎች እርስበርሳቸው ትይዩ የሚሆኑበት ቦታ ቢኖርም)፤ ልብ ሊባል የሚገበው ነገር ደግሞ በባቡር ሀዲዱ ውስጥ ያለው ሁለተኛው ሀዲድ

ከመጀመሪያው ሀዲድ በተሻለ ሁኔታ ጠንካራ እንደሆነ ማሰብ ነው። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥሞችም ውስጥም ትይዩነት ብዙውን ጊዜ የሚሠራው በዚህ መንገድ ነው።

ስለ ትይዩነት ማሰብ የሚገባን መንገድ እንደ ገደል ማሚቶ ተከታትሎ የሚያስተጋባ መሆኑንም ነው። ብዙውን ጊዜ ሁለተኛው መስመር የሚያስተጋባው እንደ መጀመሪያው መስመር ገደል ማሚቶ ነው። በ "መደበኛው" ገደል ማሚቶ አንድ ሰው የሆነ ነገር ብሎ ሲጮህ ምላሽ ሰጪው ገደል ማሚቶ በትክክል ተመሳሳይ ቃላትን ይጠቀማል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥም የሚያስተጋባው በአንድ ዓይነት ወይም በተመሳሳይ ቃላት በመጠቀም ላይሆን ይችላል። ምንም እንኳን ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ሁለተኛው መስመር ከመጀመሪያው መስመር የተለየ ነው። ሆኖም ብዙውን ጊዜ በሆነ መንገድ ትንሽ ጠንከር የሚል ነው።

ለምሳሌ ከመዝሙራት ውስጥ አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኔ እንመልከት። በተለይም ሁለተኛው መስመር በመጀመሪያው መስመር ላይ የተገለጹትን ሃሳቦች እንዴት እንደሚደግም ልብ ይበሉ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ጠንካራ ቃላትን ይጠቀማል።

*አቤቱ በቁጣህ አትቅሠፈኝ*
*በመዓትህም አትገሥጸኝ!* **መዝሙር 38፡1**

እንደገና ልክ እንደ ሁለት የባቡር ሀዲዶች ትይዩ እንደሆኑ በ **መዝሙር 38፡1** ያለው ሁለተኛው መስመር ከመጀምሪያው መስመር ጋር ትይዩ ነው። ይህም ደግሞ ጥቅም ላይ በዋሉት ቃላት ጭምር ይታያል። ቃላቶቹም በግልጽ እርስ በርሳቸው የሚመሳሰሉ ናቸው። በመጀምሪያው መስመር ላይ ያለው " በቁጣህ አትቀጽፈኝ" የሚለው ቃል በሁለተኛው መስመር ላይ " በመዓትህ አትገሥጸኝ" እንደሚለው ቃል ነው። ነገር ግን "በመዓትህ" የሚለው ቃል "በቁጣህ" ከሚለው ቃል የበለጠ ጠንካራ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። ስለዚህ በድጋሚ ማለት የምንፈልገው ሁለቱም የግጥም መሥመሮች እንደ ባቡር ሀዲድ ናቸው እርስ በርሳቸው ትይዩ ናቸው ነገር ግን "ሁለተኛው የባቡር ሀዲድ" ከመጀምሪያው ባቡር ሀዲድ የበለጠ ጠንካራ ሆኖ ይታያል። በተመሳሳይ መልኩ በ**መዝሙር 38፡1** "አትገሥጸኝ" የሚለው ቃል በመስመር አንድ "አትቅሠፈኝ" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። እንደዚሁም በመስመር ሁለት ላይ ያለው "በመዓትህ" የሚለው በመስመር አንድ "በቁጣህ" ከሚለው ቃል ጋር ትይዩ ነው። ነገር ግን በትይዩነት እንደሚጠበቀው "በመዓትህ" የሚለው ቃል "በቁጣህ" ከሚለው ቃል ጋር ትይዩ ቢሆንም "በመዓትህ" የሚለው ግን የበለጠ ጠንካራ ነው።

በ**ሆሴዕ 6፡2** ላይ ሌላ ተመሳሳይነት ያለው ምሳሌ ደግሞ እንመልከት፡-

*ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል፤*
*በሦስተኛውም ቀን ያስነሣናል፤ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን።*

በሁለተኛው መስመር ("ሦስተኛው ቀን") በሚል የተጠቀሰው ቁጥር በመጀመሪያው መስመር ላይ ("ሁለት ቀን") ተብሎ ከተነገረው ቁጥር እንዴት እነደሚበልጥ ልብ ይበሉ። እንዲህ አይነቱ የቁጥር አጠቃቀም መንገድ በትይዩ ግጥሞች የተለመደ ነው። ሁለተኛው ቁጠር ከመጀመሪያው ይበልጣል። ይህም (በ**ምሳሌ 6፡16**) "እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው፤ ሰባትንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፋለች፤" የሚለው ጥሩ አድርጎ ያብራራልናል። እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ወይም ሰባት ነገሮች እንደሆኑ ግራ አያጋባም። ሁለተኛው መስመር ከመጀመሪያው መስመር ጋር ትይዩ ነው፤ ነገር ግን የመጀመሪያው መስመር በሆነ መንገድ ሲያጠናክረው እናያለ። (እነደዚሁም እግዚአብሔር "በሚጠላው" እና በእርሱ ዘንድ "አጸያፊ" በሆነው ነገር መካከል ያለውን እድገት አስተውል። የሁለተኛው ገለጻ የበለጠ ጠንካራ ነው።

እግዚአብሔር ነቢያት በቅኔ እንዲታመኑ ለምን አነሳሳቸው? ለዚህ ጥያቄ መናልባት ብዙ መልሶች ሊኖሩ ይችላሉ። አንደኛው መልስ የነቢያት መልእክት ባህሪ ቅኔን ማካተት ይፈልጋል የሚል ነው። ምክንያቱም ሕዝቡ በሙሴ ውስጥ የተጻፍትን ቃላት አይሰሙም ነበርና። ይህም ማለት ደግሞ እግዚአብሔርን አይሰሙም ነበር ማለት ነው! ለዚህም ነው በነቢያት ውስጥ እግዚአብሔር የበለጠ ጠንክር ያለ ነገር የሚናገር የጽሑፍ ዓይነት የተጠቀመው። በአንድ ነገር ላይ ከፊት ይልቅ ጎላ ያለ ድምፅ እደመጨመር ማለት ነው። ሰዎች አይሰሙም ስለነበር እግዚአብሔር ደግሞ "የበለጠ" እና ችላ ለማለት አስቸጋሪ የሆነ የንንግግር ቅርጽ ለመጠቀም ተገዶ ነበር።

የትይዩነት አካል የሆነው የማያቋርጥ ድግግሞሽ በተለይም አንድን ነጥብ ለማጉላት በጣም ተስማሚ ነው። ዋና ነጥቦቹ በጠንካራ እና የበለጠ ጠንካራ በሆኑ ቃላት ደጋግመው ይናገራሉ። ሌላው ምክንያት ግጥም ከመደበኛ ንግግር ይልቅ አስደንጋጭ የሆኑ ቃላትን ይጠቀማል።የቃላቱ አስደንጋጭ ተፈጥሮ ደግሞ ግጥሞቹን ችላ ለማለት አስቸጋሪ ያደርገዋል። የመጨረሻው ምክንያት ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ግጥም ቃላት የማይረሱ መሆናቸውን ጭምር ነው።



## 19. ለምን ነቢያት ይህን ያህል ጠንካራ ቋንቋ ይጠቀሙ ነበር?

የነቢያት ቋንቋ አጠቃቀም አንባቢን ለማስደንገጥ በታቀደ መንልኩ ነበር። ሕዝቡ ከዚህ በኋላ "በተለመደ" ቃላትን የሚነገረው ስለማይሰማ ነቢያት በመደበኛነት የሚጠቀሙባቸው በጣም ጠንካራ ቃላት መረዳት በመቻላቸው ነው። ስለዚህ ሰዎች "የተለመደ" ቃላት ስለማይሰሙ ነቢያት መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ ጠንከር ያሉ ቃላትን ለመጠቀም ተገደዱ። እነዚህንም ጠንካራ ቃላት ብዙውን ጊዜ **ዘይቤዎች** ናቸው። ደግሞም እነዚህ ቃላት አንድን ነገር ከሌላ ነገር ጋር በማነፃፀር የሚገልጹ ናቸው። ለምሳሌ ያህል አንድዳንድ ጊዜ እሥራኤል እንደ ወይን ትገለጻለች፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ ግትር አህያ ትገለጻለች። ነቢያት ዘይቤያዊ ንግግሮችን በመጠቀም ጠበብት ነበሩና።

ለምሳሌ ያህል የእሥራኤል ሕዝብ ጣዖትን ያመልኩ ነበር። ስለዚህ ስለ ሚያደርጉት ኃጢአት የተደጋገመ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷዋቸው ነበር። ነቢያትም ደግሞ ለሕዝቡ ስለ ጣዖት አምላኪነታቸው ለማስጠንቀቅ ሲባለ እና ንስሐም እንዲገቡ ለመማጸን ተልከውላቸው ነበር። በመሠረቱ ነቢያት የእሥራኤል የመጨረሻ ተስፋ ነበሩ። እሥራኤላውያን በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈላቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ላለመስማት ለብዙ፣ብዙ ዓመታት እንቢ ብለው ኖረዋል። እንደዚሁም ደግሞ ቀደም ባሉት ነብያት የመጣውን የእዚአብሔርን ቃል ለማስማት ፈቃደኞች አልነበሩም። ለዚህም ነው በኋላ ላይ ነቢያት ቸል ሊሉት በማይችሉት ጠንካራ እና አስደንጋጭ ቃላቶችን በመጠቀም ለመናገር የተገደዱት።

ለምሳሌ ነቢዩ ሆሴዕ የተላከው እሥራኤልን ስለ ጣዖት አምልኮዋ በተመለከተ ለማስጠንቀቅ ነበር። ስለዚህ በቀላሉ "ከጣዖት አምልኮት ተመለሱ" ማለት ይችል ነበር። እንደዚህም ዓይነት መልዕክቶች ደግሞ የእግዚአብሔር የማዳን ጸጋ በሆነላቸው ነበር። ይሁን እንጂ ስለማይሰሙ ሆሴዕ ግን ለእሥራኤል ስለ ጣዖት አምልኮት ሲናገር እነዚህን "የተለመዱ" ቃላት አልተጠቀመም። ቢናገርም እሥራኤል አይሰማም ነበርና። ስለዚህ ሆሴዕ የሕዝቡን ድርጊት ከጣዓት አምልኮ የበለጠ አስደንጋጭ የሆነውን ለመግለጽ አንድቃል ሲጠቀም እንመለከታለ። በመሆኑም ሕዝቡ **ሸርሙጣ** መሆኑን ያውጃል። ሆሴዕ የተጠቀመባቸው እነዚህን የመሰሉ ቃላት የሕዝቡን ቀልብ እንደሚስቡ ምንም ጥርጥር የለውም ነበር!

እስቲ የእሥራኤል ጣዖት አምልኮ የሚገልጹትን የሚከተሉትን የግጥም ስንኞችን ይመልከቱ። ደግሞም እስቲ በሆሴዕ ዘመን እንደኖረ እሥራኤላዊ ሆነው እነዚህን ቃላት እንደሰሙ ያስቡ፡-

*እናታችሁ ሚስቴ አይደለችምና እኔም ባልዋ አይደለሁምና*
*ተምዋገቱ ከእናታችሁ ጋር ተምዋገቱ፤*
*ግልሙትናዋንም ከፊትዋ*
*ምንዝርናዋንም ከጡቶችዋ መካከል ታስወግድ ...*
**ሆሴዕ 2፡4** (በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዶሶች የተጠቀሰው ቁጥር 2 ላይ ነው)

ሆሴዕ እሥራኤል እንደ ሴትኛ አዳሪ (ጋለሞታ) እየገለጻት ነው፣ የእነዚህን የግጥም መስመር ክብደት ለመረዳት አንድ ሰው እናቶትን በዚህ መልኩ እንደገለፃት ያስቡ! ስለዚህ ሕዝቡ ተቆጥቶ ነቢያትን ለመግደል መፈለጋቸው ምንም አይስደንቅም። የነቢያቱ ጠንከር ያሉ ቃላት ሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልዕክት መስማት እንዲችሉ በጥልቀት ለመቁረጥ የታለመ ነበር። እግዚአብሔር ራሱ ነብያትን ሲልክ እንደዚህ ያደርግ እነደነበረ ተናግሯል። ቀጥሎ ያለው ደግሞ የግጥም ስንኞች አስቡ (ይህ የሶስት የግጥም ስንኞች ምሳሌ ሲሆን አንዱ ከሌላው ጋር ደግሞ ትይዩ ነው)።

*ስለዚህ በነቢያት እጅ ቆረጥኋቸው፤*
*በአፌም ቃል ገደልኋቸው፤*
*ፍርዴም እንደ ብርሃን ይወጣል፤* **ሆሴዕ 6፡5**

በብሉይ ኪዳን ዘመን ይንኖሩ የነበሩት ሰዎች እነዚህን ጠንካራ ቃላት መስማት ነበረባቸው። እንደዚሁም ደግሞ በዚህ ዘመንም የሚኖሩ ሰዎች እንዚህን ጠንካራ ቃላት መስማት ያስፈልጋቸዋል። ይህ ጠንካራ ቋንቋ በብሉይ ኪዳን በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ጥቅም ብቻ እንዳልነበረ ማስታወስ ጠቃሚ ነው። በዚህ ዘመንም ያሉ ስዎች እነዚህን የመሳስሉት ተመሳሳይ ቃላት መስማት አለባቸው። ብዙ ጊዜ በግድ የለሽነት ከሚመጣ ድንጋጤ ልንወጣ ያስፈልገናልና።


ነቢያት

የነቢያት ቃል ከእግዚአብሔር ከራሱ የሚመጣ ነውና። ነቢያት ሰዎች የእግዚአብሔርን መልካም ቃል እንዲሰሙ፣ ንሰሐም እንዲገቡ እና ለእግዚአብሔርም በመታዘዝ እንዲሄዱ የሕዝቡ ትኩረት ለመሳብ በጥንቃቄ የተመረጡ ናቸው (**ዕብራውያን 4፡12** ይመልከቱ)።



## 20. የብሉይ ኪዳን ነቢያት ያልተሟላ እውቀት

ምንም እንኳን የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከክርስቶስ መምጣት በፊት የኖሩ ቢሆኑም፤ ሁሉም ነቢያት ስለ ክርስቶስና ስለ መንግሥቱ አውቀው ስለ እርሱ ተናግረው ነበር (**ሉቃስ 24፡25–27፣ 44–48፤ የሐዋሪያት ሥራ 3፡18–26 እና 1 ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ)። ስለዚህም ምንም እንኳን **በብሉይ ኪዳን** የሚኖሩ አማኞች ቢሆኑም እንኳን ነቢያት ስለ **አዲስ ኪዳን** ዘመን ይናፍቁ፣ ይናገሩ እና ይጽፉም ነበር። ደግሞም የእግዚአብሔር ተስፋዎች በክርስቶስ ዘመን እንደ ሚፈጸሙ ያውቁ ነበር፤ እናም በክርስቶስ ዘመን ለመኖርም ይመኙ ነበር (**ማቴዎስ 13፡17**)። ይሁን እንጂ ስለ ክርስቶስ በእርግጥ ቢናግሩም የነቢያት እውቀት ግን የተሟላ አልነበርም። ስለክርስቶስ የበለጠ ለማወቅ ይፈልጉ ነበርና፤ ነገር ግን በሙሴ መጽሐፍ ማለትም (ከዘፍጥረት– ዘዳግም)፣ እንደዚሁም በሌሎች በተጠናቀቁ የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች እና እግዚአብሔር በግል የገለጠላቸውን ብቻ ያውቁ ነበር። ይህ ማለት የብሉይ ኪዳን ነቢያት የማያውቋቸው ስለ ክርስቶስ የተወሰኑ ዝርዝር ጉዳዮች ነበሩ ማለት ነው። ስለ ክርስቶስ ያለውን እውነት በብሉይ ኪዳን ቀስ በቀስ **በሂደት** በሆነ መንገድ ተገልጧል። ስለዚህም በኋላ ላይ የተነሱት ነቢያት በቀደሙት ነቢያት በተገለጹት ነገሮች ላይ እየጨመሩ ወይም እየገነቡ ነው የተናገሩት። ስለዚህ አንባቢው በብሉ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ እያነበበ ሲቀጥል የክርስቶስ ሥዕል ይበልጥ ግልጽ እየሆነለት ፍንትው ብሎ ይታየዋል ማለት ነው።




## 21. የሐዋሪያት ሙሉ እውቀት


በአዲስ ኪዳን ሐዋሮያትም ሆኑ በብሉ ኪዳን የነበሩት ነቢያት የጻፉት ስለ ክርስቶስ ነው። ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያን "በሐዋሪያትና በነቢያት መሠረት" ላይ የተመሰረተችው (**ኤፌሶን 2፡20** ይመልከቱ)። በዚህ በኤፌሶን ክፍል ሐዋሪያት በመጀመሪያ የተጠቀሱት የነቢያት ተርጓሚ በመሆናቸው ነው። ሐዋሪያት ነቢያትን እንዲረዱ ትክክለኛውን መንገድ ለአንባቢዎች የሚያሳዩ ናቸው። ምንም እንኳን የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ ክርስቶስና ስለ መንግሥቱ ቢጽፉም አንባቢ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ ክርስቶስ የተናገሩትን መልዕክት ሁሉ በአዲስ ኪዳን ስለ ክርስቶስ እንደተጻፈው ዓይነት ግልጽ እንዲሆንለት መጠበቅ የለበትም። ሐዋሪያት ክርስቶስን በቅርብ በዓይናቸው አይተውታል። በእጃቸው ዳሰውታል። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ግን ክርስቶስን አላዩትም ነበር። በእርቀት ስለሚያውቁት ስለ አንድ ነገር እንደሚተርኩ ሰዎች ናቸው እንጂ። አንድን ነገር በሩቅ የሚያይ ሰው በሩቅ ስለሚያየው ሰው ዋና ዋና ዝርዝሮችን ማየት ይችል ይሆን ይሆናል፤ ነገር ግን አንዳንድ ጥቃቅን ዝርዝሮች ይበልጥ ግልጽ የሚሆኑለት የሚገለጸው ነገር በቅርበት መመልከት ሲችል ብቻ ነው።

በተጨማሪ ደግሞ የነቢያት መልዕክት ፍጹም እውነት ነው፤ ነገር ግን ነቢያት የኖሩት እነሱ የሚገልጹት ክስተቶች ከመከሰታቸው በፊት ነበር። ስለዚህ አንባቢ ነቢያት ስለክርስቶስ እና ስለ ወንጌል ክስተት የተናገሩት ዝርዝር ጉዳዮች **ግልጽነት የጎደለው** ሊሆን እንደሚችል መጠበቅ ይኖርበታል። ይህ ግልጽነት ማጣት በእውነቱ ለአንባቢ የተሰጠ ስጦታ ነው። ነቢያት ክርስቶስንና መንግሥቱን የሚገልጹበት የተለያዩ የግጥም መንገዶች እንዲጠቀሙ አስገድዷቸዋልና። ስለ ክርስቶስ የተነገሩ የብሉይ ኪዳን ግጥሞች ውበት ግሩም ነው። ከዚህ በተጨማሪ በግጥም መልክ በመሆናቸው ምክንያት ለማስታወስ ቀላሎች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ከአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ይልቅ ለመረዳት ከበድ የሚሉም ናቸው። እንዳውም ከሐዋሪያት መልዕክት ያለፈ ጥልቀትና ትርጓሜ ያላቸው ናቸው። ግጥም በባሕሪው ወደ ሰው ልብ ውስጥ ዘልቆ በመግባት እና ጥልቅ ስሜቶችን በማነሳሳት የታወቀም ነው። የብሉይ ኪዳን የክርስቶስና የመንግሥቱ መግለጫዎች ለአዲስ ኪዳን አማኞች በጣም የሚያበረታቱ ናቸው። ነቢያት እግዚአብሔርን ለሚወድ ለኋለኛው ትውልድ እንደጻፉ ያውቁ ነበር። እነዚህ የኋለኞቹ ትውልዶችም መልዕክቶቻቸውን እንደ ሚያነቡና በመልዕክቶቻቸውም ውስጥ ተስፋና ማበርታቻ እንደሚያገኙ ደግሞ ያውቁ ነበር።

ስለዚህም የብሉይ ኪዳን ትንቢት ማንበብ የአዲስ ኪዳን መልዕክት እንደማንበብ አይደለም። በመልዕክቶች ውስጥ የምናገኛቸው ጽሑፎች በጣም እጥር ምጥን ያሉ ናቸውና። ብዙውን ጊዜም ከብሉይ ኪዳን ይጠቅሳሉ ደግሞም ትርጉሙንም ያብራራሉ። ነገር ግን በብሉ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍት ውስጥ ያሉት ጽሑፎች በአዲስ ኪዳን መልዕክት ውስጥ እዳሉት እጥር ምጥን ያሉ አይደሉም። የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች እንደ ሙዚቃ ትሪዒት የበለጠ ሰፋ ያሉ ናቸው። የነቢያት መልዕክት ጠንካራ ስሜትን ለመቀስቀስ የታሰቡ ናቸው እንጂ እጥር ምጥን ያለ አጭር መልዕክት እንዲያስተላልፉ የታቀዱ አይደለምና።

የነቢያት መልዕክት በወቅቱ በሰሙት ሰዎች ሁሉ ላይ እምነትንና ተስፋን ሊቀሰቅስ ይገባ ነበር። መልዕክቶቻቸውም ሰዎችን ለክርስቶስ መምጣት ማዘጋጀት ነበረበት። እንዲያውም ብሉይ ኪዳን ስለክርስቶስ መሆኑን ባለመረዳታቸው ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን “ልባችሁ ከማመን የዘገየ” በማለት ገሥጻቸው (**ሉቃስ 24፡25–27** ይመልከቱ)። ይህ ማለት ግን ሁሉም ሰዎች ነቢያትን ለመረዳት በልባቸው የዘገዩ ነበሩ ማለት አይደለም! ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች የነቢያትን ቃል አምነው ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ሊገናኙት ተዘጋጅተው እንደነበር ግልጽ ነው። ለምሳሌ ሁለቱም ማለት የኢየሱስ እናት ማርያም እና የመጥመቁ ዮሐንስ አባት ዘካሪያስ በብሉይ ኪዳን ስላሉት ተስፋዎች በጥልቀት ያስቡ ነበር፤ ይህም በክርስቶስ መምጣት የነበራቸው ተስፋና መጠባበቅ ያዳበረ ሆኖላቸዋል (**ሉቃስ 1፡46–55** እና **67–79** ይመልከቱ)።






## 22. የትንቢተ ኤርምያስ መጽሐፍ

የትንቢተ ኤርምያስ መጽሐፍ በሁለተኛው የነቢያት ክፍል (**የማብራሪያ** መጻሕፍት) የመጀመሪያው መጽሕፍ ነው። ይሁን እንጂ ኤርምያስ በዚህ በሁለተኛው የነቢያት ክፍል እንደ መጀምሪያ መጽሐፍ መቀመጡ የኤርምያስ ትንቢት በዚህ ክፍል ውስጥ በጣም አስፈላጊ መጽሐፍ ስለሆነ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ሁሉም መጻሕፍት "የእግዚአብሔር እስትንፋስ" ያለባቸውና አስፈላጊ ናቸው (**2 ጢሞቴዎስ 3፡16** ይመልከቱ)። እንደዚሁም ኤርምያስ በዚህ ክፍል መጀመሪያው መጽሐፍ ሆኖ መቀመጡ ኤርምያስ በዚህ ክፍል ውስጥ የመጀመሪያው ነቢይ ስለሆነም አይደለም። እንዲያውም ዮናስ፣ አሞጽ፣ ሆሴዕ፣ ኢሳይያስ፣ሚክያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም እና ሶፎንያስ ሁሉም ከኤርምያስ በፊት ትንቢት የተናገሩ ናቸውና።

በዚህ የነቢያት ክፍል ውስጥ ረጅሙ መጽሐፍ ትንቢተ ኤርምያስ ስለሆነ መጀመሪያ ላይ የተቀመጠው ለዚህ ይመስላል። መጽሐፍቶቹ መጀመሪያ የተጻፉት በጥቅልሎች ላይ ነው፤ በመሆኑም ጥቅልል የሚያዘጋጀው አካል መጀመሪያ ረጅሙን ሥራ ያስቀምጣል፤ ይህም መጽሐፉን በሙሉ በአንድ ጥቅልል ለመያዝ የሚያስችል በቂ ቦታ እንዳለ ማረጋገጥ ይኖርበታል ማለት ነው። ጥቅልሉ በአጭር መጽሐፍ የጀመር ከሆነ ደግሞ ረጅሙ መጽሐፍ በአንድ ጥቅልል ለመጨረስ በቂ ቦታ ላይኖርው ይችላልና።


ኤርምያስ በ627–580 ዓክልበ መካከል ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው። መልዕክቱ የጻፈው በይሁዳ ለሚኖሩ ሰዎች ሲሆን በዋንኛነት ኃጢአታቸው ሊያስከትለው የሚችለውን መዘዝ ያስጠነቅቃቸውና ስለመጪው ጊዜ ይናገር ነበር። እንደ ሌሎች ነቢያትም ሁሉ ኤርምያስም ስደት ድርሶበታል። ደግሞም ስለ አዲሱ ኪዳንም ጽፏል (**ኤርምያስ 31፡33–34** ይመልከቱ)። ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ "ሁለተኛው ዘጸአት" ጽፏል (**ኤርምያስ 16፡14–15** እና **ኤርምያ**ስ **23:7–8** ይመልከቱ)። ኤርምያስ ይህን ሁለተኛው ዘጸአት ከዳዊት ቤት ከሚመጣው ንጉሥ ጋር አያይዞታል (**ኤርምያስ 23፡5–6** ይመልከቱ)። በእርግጥም ይህ ንጉሥ ከዳዊት ወገን መጥቷል። ስሙም ኢየሱስ ነው (**ማቴዎስ 1፡1** ይመልከቱ)!



## 23. የትንቢተ ሕዝቅኤል መጽሐፍ

የትንቢተ ሕዝቅኤል መጽሐፍ ደግሞ በሁለተኛው የነቢያት ክፍል (ማብራሪያ መጻሕፍት) ውስጥ ሁለተኛው መጽሐፍ ነው። እንደዚሁም ደግሞ በዚህ ክፍል ውስጥ ሕዝቅኤል ሁለተኛው መጽሐፍ ሆኖ የተቀመጠው ሕዝቅኤል በዚህ ክፍል ውስጥ ቀየት ካሉት ነቢያት ሁለተኛው ስለሆነ አይደለም። ምክንያቱም ብዙዎች ነቢያት ከሕዝቅኤል በፊት ትንቢት ተናግረዋልና።በዚህ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ያሉት የነቢያት መጽሐፍት በጊዜ ቅደም ተከተል የተደረደሩ ደግሞ አይደሉም። በዚህ በሁለተኛው ክፍል ሕዝቅኤል ሁለተኛው መጽሐፍ የሆነበት ምክንያት ረጅሙ ሁለተኛው መጽሐፍ በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም።


ሕዝቅኤል ካህንና ነቢይ ነበር። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ593–570 ዓክልበ መካከል ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው። መልዕክቱንም የተጻፈው ለይሁዳ ሰዎች ነው። መልዕክቱም የተጻፈው ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱ ከመፍረሳቸው ጥቂት ቀደም ብሎና እንደዚሁም ከፈረሱም ጥቂት ጊዜ በኋላ ነው። የሕዝቅኤል መልዕክት ቦታቸው የፈረሰባቸውና ቤተ መቅደሳቸውን ላጡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ተስፋ የሚሰጥ ነው። ሕዝቡ እግዚአሔር አሁንም ለእነሱ አላማ እንዳለው ወይም ትቶዋቸው እንደሆነ ያስቡ ነበር። ስለዚህ ልክ እንደ ኤርምያስም፤ ሕዝቅኤልም ስለ የሁለተኛው ዘጸአት ክስተት ተናግሮ ነበር (**ሕዝቅኤል 34፡11–16** እና **ሕዝቅኤል 36:22–38** ይመልከቱ)። ሕዝቅኤል ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ዳግም ልደት (**ሕዝቅኤል 37፡1–14**) እና ሕይወታቸው ከዳዊት ዘር በሚመጣው ንጉሥ ሥር ምን እንደሚመስል ጽፏል (**ሕዝቅኤል 37:15–28** ይመልከቱ)። ደግሞም ሕዝቅኤል የእሥራኤል ጠላቶች ውድቀት በተመለከተም ተናግሯል (**ሕዝቅኤል 38–39** ይመልከቱ)። እንደዚሁም ደግሞ ወደፊት ስለሚገነባውም አዲስ ቤተ መቅደስ ተናግሮ ነበር (**ሕዝቅኤል 40–48** ይመልከቱ)። ኢየሱስ ለሰዎች የሚያመጣውን ሕይወት እና የመንፈስ ቅዱስ ሥራን በተመለከተ ሲገልጽ በዚህ የሕዝቅኤል ክፍል ውስጥ ያለውን ቋንቋ ተጠቅሞበታል። እንደዚሁም ደግሞ ሐዋሪያው ዮሐንስ በ**ራዕይ 21–22** ስለ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በተመለከተ በሰጠው ማብራሪያ ላይም የሕዝቅኤልን ብዙ ቃላቶችና ሥዕላዊ መግለጫዎች ተጠቅሟል።



## 24. የትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ

የትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ ደግሞ በሁለተኛው የነቢያት ክፍል (**ማብራሪያ** መጻሕፍት) ውስጥ ሦስተኛው መጽሐፍ ነው። እንደዚሁም ደግሞ የኢሳይያስ መጽሐፍ በነቢያት ክፍል ውስጥ ሦስተኛው ረጅሙ መጽሐፍ ነው። ኢሳይያስ በ740–700 ዓክልበ መካከል ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው። ለይሁዳ ሰዎች ወደ ባቢሎን ከመማረካቸው በፊት ይጽፍላቸው ነበር። ሆሴዕ ምንም እንኳን አገልግሎቱ በእሥራኤል ውስጥ ለነበሩ ሰዎች ቢሆንም ከኢሳይያስ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው። እንደዚሁም ነቢዩ ሚክያስም  በተማሳሳይ ጊዜ ትንቢት ተናግሯል። በእርግጥም ደግሞ ኢሳይያስ እና ሚክያስ ተመሳሳይ የመልዕክት ክፍል አላቸው (**ሚክያስ 4፡1–5** ከ **ኢሳይያስ 2፡1–5** ጋር ያመሳክሩ)። ይህም ማለት ከእነዚህ ሁለት ነቢያት አንዱ (ኢሳይያስ ወይም ሚክያስ) የሌላውን ነቢይ ቃል ሰምቶ መልዕክቱ ቀጥታ ይጠቀም ነበር ማለት ነው! ይህም ነቢያት እርስ በርሳቸው ይደማመጡ እንደነበር የሚያሳይ ማስረጃ ነው!

እንደ ኤርምያስና ሕዝቅኤልም  ኢሳይያስም ስለ ሁለተኛው ዘጻአት ተናግሯል። እንደዚሁም ደግሞ ኢሳይያስ ስለ የእግዚአብሔር "አገልጋይ" ብዙ ተናግሯል። ያም አገልጋይ ኢየሱስ ነው። በእርግጥ በኢሳይያስ ውስጥ "አገልጋዩን በተመለከተ የተጻፉ መዝሙሮች አሉ" (**ኢሳይያስ 42፡1–4፣ 49፡1–6፣ 50፡ 4–9** እና **52፡13–53፡12** ይመልከቱ)። ነብዩ ኢሳይያስ በብዙ ቦታዎች ስለክርስቶስ መምጣት እና ስለ ክርስቶስ መንግሥት ተንብዮአል (ለምሳሌ **ኢሳይያስ 9፡1–7** ይመልከቱ)። በተጨማሪም አገልጋዩ ወይም "ባሪያው" የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአት እንደሚሸከም ተናግሯል (**ኢስይያስ 53**)። ኢሳይያስ የእምነት ሰው ነበር። ደግሞም ኢሳይያስ እግዚአብሔር በራዕይ የማየት እድል ያጋጠመው ሰው ነበር (**ኢሳይያስ 6፡ 1–13** ይመልከቱ)፤ እንደዚሁም የእግዚአብሔር ተስፋዎች የሚፈጸሙበት ቀን – እግዚአብሔር ደግሞ ከሕዝቡ ጋር የሚሆንበትን ቀን ይናፍቅ ነበር (**ኢሳይያስ 64፡1–12**)። ኢየሱስ በምኩራብ ሲያስተምር **ኢሳይያስ 61** ን ጠቅሷል (**ሉቃስ 4፡16–21** ይመልከቱ)። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- "ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ"። ይህ ማለት ኢየሱስ ኢሳይያስን አንብቧል ደግሞም ኢሳይያስ የተናገረው ስለ እሱ እንደሆነ ተረድቷል ማለት ነው!



## 25. የ "አሥራ ሁለቱ" ነቢያት መጻሕፍት

የአሥራ ሁለቱ ነቢያት መጻሕፍት በአይሁዶች መጽሐፍ 12 ክፍል እንዳለው አንድ መጽሐፍ ተደርጎ ይቆጠሩ ነበር። ስለዚህ በዘመናችንም ያሉ የቅዱሳት መጽሐፍት አንባቢዎች እነዚህን 12 መጻሕፍት እንደ አንድ ክፍል ቢመለከቱት ትልቅ ጠቀሚታ አለው። በዚህ አንጻር እንደ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል ወይም ኢሳይያስም አብረው ይሠራሉ። ኢሳይያስ አንድ መጽሐፍ እንደ ሆነ ሁሉ በተመሳሳይ መልኩ እነዚህም (አሥራ ሁለቱ) አንድ መጽሐፍ ናቸው።

ሆኖም መታወቅ ያለበት፤ በዚህ አንድ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት 12 መጻሕፍት በጊዜ ቅደም ተከተል ያልተቀመጡ መሆኑን ነው። በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀመጡ ቢሆን ኖሮ ዮናስ፣ አሞጽ እና ሆሴዕ የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት ይሆኑ ነበር። ይልቁንም በአሥራ ሁለቱ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙት 12 መጻሕፍት በርዕሳቸው መሠረት የተደረደሩ ይምስላሉ። እንደዚሁም በአንድ መጽሕፍ መጨረሻ ላይ ያሉ አንዳንድ ቃላት በሚቀጥለው መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ ከሚታዩ ቃላት ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ስለዚህ መጽሐፎቹ እንዴት እንደተጣመሩ ማወቅ ለሰባኪው ደስታን ይሰጣሉ።

ትንቢተ ሆሴዕ በመጀመሪያ ላይ የተቀመጠ በመሆኑ ለጠቅላላው ለአሥራ ሁለቱ "መጽሐፍት" እንደ መግቢያ ሆኖ ያገለግላል። ስለዚህ ነቢዩ ሆሴዕ ለአንባቢያን የመጽሐፉን መግቢያ አዘጋጅ ይመስላል። በሌላው አንጻር ደግሞ ሚልክያስ የመጨረሻው መጽሐፍ ስለሆነ የአሥራ ሁለቱ "መጽሐፍት" በሙሉ መደምደሚያ ሆኖ ያገለግላል።

አንዳንድ ጊዜ በአሥራ ሁለቱ ውስጥ ያሉትን መጽሐፎች "ትንንሽ ነቢያት" በመባልም ይታወቃሉ። ሆኖም ይህ ማለት "ከዋንኞቹ ነቢያት" ማለትም (ከኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል እና ከኢሳይያስ) ያነሱ ናቸው ማለት ግን አይደለም። በአንጻሩ ይህ ማለት ደግሞ እንደ "ዋንኞቹ ነቢያት" ረጃጅም አይደሉም ማለት ነው። "ቅዱሳት መጽሐፍት ሁሉ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለባቸው ናቸው" ስለዚህ ሁሉም አስፈላጊ ናቸው ማለት ነው (**2 ጢሞቴዎስ 3፡16 ይመልከቱ**)። በአሥራ ሁለቱ ውስጥ የሚገኙት ትናንሽ መጻሕፍትም ጭምር የእግዚአብሔር እስትንፋ ያለባቸው ናቸውና። ሁሉንም ቅዱሳት መጻሕፍት ለእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ አስተዋጻዖ ያደርጋሉ ማለት ነው።

እንደዚሁም ደግሞ ልክ እንደ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል እና ኢሳይያስም አሥራ ሁለቱ መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ሁለተኛው ዘጸአት፣ ስለክርስቶስ መምጣት፣ ስለክርስቶስ መንግስት እና የእግዚአብሔር ጠላቶች መሸነፍ ይናገራሉ። እነዚህ መጻሕፍት እያንዳንዳቸው "ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማሉ" (**2 ጢሞቴዎስ 3፡16** ይመልከቱ)። ለዚህም ነው ሐዋሪያት በአሥራ ሁለቱ ውስጥ ከሚገኘው የትንቢት መልዕክቶች በተደጋጋሚ የጠቀሱት።

**በአሥራ ሁለቱ ውስጥ የተገለጹት ነቢያት እያንዳንዳቸው የተነበዩበት ግምታዊ ጊዜ ወይም ዘመን ከዚህ በታች ተዘርዝሯል፦**

ሆሴዕ – ከ 760–730 ዓክልበ

ኢዩኤል – ምናልባትም በ 600 ዓክልበ

አሞጽ – በግምት 760 ዓክልበ

አብድዩ – ምናልባት በ 586 ዓክልበ

ዮናስ – በግምት 770 ዓክልበ

ሚኪያስ – ከ 737–690 ዓክልበ

ናሆም – በ 650 ዓክልበ አካባቢ

እንባቆም – በ 639 ዓክልበ አካባቢ

ሶፎኒያስ – በ 627 ዓክልበ አካባቢ

ሐጌ – በ 520 ዓክልበ አካባቢ

ዘካሪያስ – ከ 520–518 ዓክልበ

ሚልክያስ – በግምት 433 ዓክልበ